CALGARY ETHIOPIAN COMMUNITY ASSOCIATION

# HIBRET

# ሕ ብ ረ ት

A Tribute to the Calgary Ethiopian Community Association 40 Year Anniversary

ለካልጋሪ የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ማኅበር የ40 ዓመት ክብረ በዓል የተዘጋጀ



1983

40

2023



**SPECIAL EDITION**

**ልዩ ዕትም**

September 2023



Immigrant Outreach Society (IOS)
Active Community Engagement

## ABOUT US

Immigrant Outreach Society is a non-profit organization that provides evidence-based, language-specific,and culturally appropriate mental health and psychosocial interventions for refugees from East Africa. IOS also promotes racial equity,inclusion,and cultural awareness in public policies and systems.

## ስለ እኛ

ኢሚግራንት አውትሪች ሶሳይቲ ከምስራቅ አፍሪካ ለመጡ ስደተኞች በቋንቋቸው እና ባህላቸውን ያተኮረ የማህበራዊ እና ስነልቦናዊ ድጋፍ እና አገልግሎት የሚሰጥ የትራደኦ ድርጅት ነው። በተጨማሪም ማህበረሰባችን ከዘረኝነት ጫና ወይም አድሎ ነጻ ሆኖ እንዲኖር የዘር ኢፍትሃዊነትን ያነጣጠሩ የማህበረሰብ ፕሮግራሞች ላይ እንሰራለን።

## OUR ACTIVITIES

- Culturally appropriate, language-specific and trauma-informed psychosocial and mental health programs.
- Crisis response and intervention programs.
- Family andYouth wellness support programs.
- Wellness supports and programs for women, domestic violence survivors, and essential workers.
- Community program and initiatives targeting antiracism and racial injustice.


## CONTACT US

Phone: 403-400-4782

Email: info@ioscalgary.org

https://www.immigrantoutreachsociety.ca

# Table of Contents

Message from the President ........................................ 1
Editorial ........................................ 7
ቆይታዬ ከቀድሞ የስራ አመራር አባል ........................................ 9
እምቦቀቅላዉ ........................................ 10
የኮምኒቲ እይታ ........................................ 10
የማህበራዊ ሜዲያ ተጽእኖ ........................................ 17
*እናንተ እኔን ብትሆኑ?* ........................................ 18
Interview with Dr. Alula Damte ........................................ 19
"አሁንለምንድነው ፈሪ ማቀንቀኑ ቅጠል አይበጠስ ካልደረሰ ቀኑ!" ........................................ 21
በፍጥነት ሥራ  ለማግኘት ትፈልጋለህ? ........................................ 22
የዕፅዋት የሚስጥር ቋንቋ ........................................ 24
How Ethiopia Tracks Date and Time ........................................ 26
Interview with Sileshi Mekonnen ........................................ 26
Interview with Samuel Tadesse ........................................ 33
የማራዶናና የፔሌ ልዩነት ........................................ 34
ስለሀበሻ ዩናይትድ ስፖርት ክለብ በጥቂቱ ........................................ 35
ስለማህበሩ ታሪክ ትዝ የሚለኝ ........................................ 35
ከዚህም ከዚያም ........................................ 36

**የካልጋሪ የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ማህበር የተመሰረተበትን 40ኛ አመት ክብረ በአል ለማሰብ የተዘጋጀ ልዩ እትም**

**A Special Issue to Mark the 40th (1983 – 2023) Anniversary of the Calgary Ethiopian Community Association**

**September 2023, Calgary, Alberta, Canada**

**Special Thanks to Our Sponsors and to those Volunteers who helped us complete this Issue**

**Copyright© 2023, Calgary Ethiopian Community Association, 1420 40th Avenue NE, Unit 14, Calgary, AB, T2E 6L1**

# BOLE EXPRESS INC.

- Air Freight
- Sea Freight
- Custom Clearing
- Pickup & Deliveries

Ethiopian
የኢትዮጵያ
THE NEW SPIRIT OF AFRICA

ETHIOPIAN

## የምንሰጣቸው አገልግሎቶች


- የፖስታ ጥቅሎች
- መኪናዎች
- የመኪና እና የከባድ ማሽነሪ መለዋወጫ
- የቤት እና የቢሮ እቃዎች
- የኮንስትራክሽን እቃዎች
- ኮንቴነሮች እና የተለያዩ እቃዎችን በቅናሽ ዋጋ ወደ ኢትዮጵያ እንልካለን!!!

ብር በተሻለ ዋጋ ወደ ኢትዮጵያ እንልካለን!!!

Tel:- 403 918 8678
Email:- sol_ethio2010@yahoo.com

# Message From the President

የካልጋሪ የኢትዮጵያ ማኅበረሰብ ማህበር ከተቋቋመ ይኸዉና 40 ዓመት ሆነ። በነዚህ አመታት ዉስጥ ማህበሩ ቀለል ካለ ስብስብ፣ ወደዛሬዉ በመለስተኛ ደረጃም ቢሆን የተጠናከረ ተቋም፣ በሂደት በመቀየር፤ በርከት ያሉ የበጎ አድራጎት፣ የማህበራዊና የባህል ስራዎችን አከናዉኗል። ከነዚህም ዉስጥ የተቸገሩ ሰዎችን መርዳት፣ ማህበራዊ ዉይይቶችን ማዘጋጀትና ማኪያሄድ፣ በልጆች የዕድገት ዙሪያና የቋንቋ ማስተማር የተሰራዉ ስራ፣ በካልጋሪ ስታምፒድና በመሳሰሉት ማህበራዊ ዝግጅቶች የሚደረገዉ ተሳትፎ፣ ከሌሎች ድርጅቶች ጋር የሚደረገዉ ትብብርና፣ ከመንግስታዊ ተቋማት ጋር ያለዉ ግንኙነት፣ በአባላት መካከል የሚደረገዉ ዉይይት፣ ተጠቃሽ ስራዎች ናቸዉ።



ዶ/ር ሉልሰገድ ይማም

ከሁሉም በላይ፣ ከ2002 ገደማ ጀምሮ፣ በየዓመቱ ለአባላት የሚሰጠዉ የስፖንሰርሽፕ አድል፣ ቀደም ብለዉ የነበሩ የማህበሩ አመራር አባላት ባንድ ወቅት ከሚመለከታቸዉ የመንግስት አካላት ጋር በመነጋገር ማህበሩን ተጠቃሚ ያደረጉበት የድካም ዉጤት ሲሆን፣ አሁንም ድረስ በርካታ በስደት ላይ ያሉ ኢትዮጵያዉያኖች የሚረዱበት ወደር የሌለዉ ቀና ተግባር ተብሎ የሚጠቀስ ነዉ። በጥቂቶች ይኽ የስፖንሰርሽፕ ጉዳይ እንደቀላል የሚታይ ቢሆንም፣ በአሁኑ ጊዜ ካለዉ ፍላጎት ጋር ሲታይና እንደዚህ አይነት እድል ለማግኘት ከሚጥሩ ሌሎች ማህበራት ልፋት ጋር ሲነጻጸር፣ የተሰራዉ ስራ ከሌሎች መደረግ ከሚገባቸዉ ነገሮችም በላይ፣ ትልቅ ስራ ነበር ማለት ይቻላል። በዚህ የስፖንሰርሽፕ ዕድል አማካኝነት በርካታ ኢትዮጵያዉያን፣ በፖለቲካ አመለካከትና በሌላ አቋማቸዉ ሲደርስባቸዉ ከነበረዉ መከራ ተላቀዋል። በትክክል ቁጥሩ ባይታወቅም፣ ይኽን ዕድል በማግኘት፣ ወደካልጋሪ መጥተዉ ኑሯቸዉን የሚመሩና የማህበሩ አባል የሆኑ ቡዙ ግለሰቦች አሉ፤ አንዳዶቹም ማህበሩን ከተቀላቀሉበት ግዜ ጀምሮ፣ ለማህበሩ ዕድገትና ጎልቶ መታየት፣ ከፍተኛ አስተዋጾ እያደረጉ ይገኛሉ።

ከእስፖንሰር እድል ባሻገር፣ ማህበሩ ከሰራቸዉ ትልቅ ስራዎች ከቅርብ ግዜ ወዲህ ገዝፎ የሚታየዉ፣ በ2019 መጨረሻ ላይ የተገዛዉ የማህበሩ ማእከል ነው። የማህበሩ ማእከል፣ 150 ያክል ሰዎች የሚይዝ አዳራሽ፣ የቦርድ ሩም፣ ዘመናዊ ቀለል ያለ ኪችን፣ የማህበሩ ጽ/ቤት፣ ትንሽ ልይብራሪ የመጀመሪያዉ ወለል ላይ ሲኖረው፣ ሰባት ያክል ቢሮዎች ደግሞ፣ ላይኛዉ ወለል ላይ ይገኛሉ። ይህ ማእከል፣ ከJanuary 2021 ጀምሮ እስከ September, 2021 ድረስ በእደሳ ላይ ቆይቶ፣ ከSeptember, 2021 ጀምሮ፣ በአገልግሎት ላይ ይገኛል። በመሆኑም፣ የማህበሩ ማእከል መገዛት፣ ማህበሩ ከተመሰረተበት ከ1982 ወይም ሬጂስተር ካደረገበት ከ1983 ጀምሮ፣ በኪራይ ሲገለገልበት ከነበረዉ በከተማዉ ማእከል ከሚገኝ ሁለት ክፍል ቢሮ፣ ከ38 አመት በኋላ እንዲወጣ ረድቷል። የማህበሩ ማእከልን መገዛትና የማህበሩ የአሰራር ክንዋኔ መስትካክልን ተከትሎ፣ የአዲስ አባላት ቁጥር እየጨመረ መጥቷል። በአሁኑ ሰአት፣ በአጠቃላይ ከ1900 በላይ አባላት፣ ተመዝግበዉ ይገኛሉ።

ከእስፖንሰርሽፕና ከማእከል ግዥ ውጭ፣ በ2019 እና በ2020፣ የCOVID19 ወረርሽኝ በአለማችን በተከሰተበት ወቅት፣ ቫይረሱ በቀጥታ ከሚያመጣዉ ጉዳት በተጨማሪ፣ ሰዎችን ክፉኛ በኢኮኖሚ ማዳከም፣ አንዱና ዋነኛዉ ችግር ነበር። በተለይ፣ በሽታዉ በርካታ ኢትዮጵያኖች ይሰሩባቸዉ በነበሩ የኢንደስትሪ ማእከሎች በብዛት ተስፋፍቶ ስለነበር፣ በማህበሩ አባላት ላይ ያደረሰዉ ጉዳት ከፍተኛ ነበር። በመሆኑም፣ የካልጋሪ የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ማህበረሰብ ማህበር፣ በካናዳ ቀይ መስቀል በኩል፣ ከካናዳ መንግስት ባገኘዉ የገንዘብ እርዳታ፣ በወረርሽኙ አማካኝነት ከስራ ተፈናቅለዉ፣ ገቢያቸዉ

ለቀነሰ ሰዎች፣ እንዲሁም፣ ልጆችን ለመጠበቅ ሲባል፣ ቤት ለዋሉ እናቶች፣ በአጣቃላይ ችግር ላይ ለነበሩ፣ በወቅቱ በተለያየ ዙር የግሮሰሪ እርዳታ፣ በዚሁ እርዳታ ፕሮግራም፣ ከግሮሰሪዉ በተጭማሪ፣ 40 ላፕቶፖችን ለ40 ቤተሰብ፣ እንዲሁም ለተለያየ ቤተሰብ ልጆች የትምህርት ቤት ቁሳቁስ መስጠታችን ይታወሳል። ይህን ሁሉ ለማህበረሰቡ ለማድረግ ለረዳን፣ በተለያየ መልኩ ለሚያግዘን፣ ከሁሉም በላይ ሀገራችን ኢትዮጵያ ዉስጥ ሰዉ እንደቅጠል በሚረግፍበት በአሁኑ ወቅት፣ እኛ ወደዚህ ሀገር በተለያየ መንገድ መጥተን በሰላም እንድንኖር ለፈቀደልን የካናዳ መንግስትና ህዝብ፣ ምስጋናችን ከፍ ያለ ነዉ።

ከዚህ ሌላ በካናዳ ከኢትዮጵያዊያን የተወለዱ ወይም ከኢትዮጵያ በልጅነታቸዉ መጥተዉ፣ ካናዳ ዉስጥ ያደጉ ወጣቶችን ለምርዳት፣ ከ2017 ጀምሮ በፌደራል መንግስት summer temporary employment program፣ ከJuy እስከ August ተማሪዎችን በመቅጠር ወጣት ኢትዮጵይዉያን ከማህበረሰቡ ጋር ያላቸዉን ግንኙነት የሚያጠናክሩበትንና ማህበሩን የሚረዱበትን ሁኔታ ለመፍጠር እየተሞከረ ይገኛል።

ከላይ ከተጠቀሱት የተለያዩ ክንዋኔዎች ዉጭ፣ ማህበሩ አልፎ አልፎ የሚደረግና በበጎ አድራጊዎች የታገዘ የቡና ጠጡ ፕሮግራም ሲያዘጋዥ ቆይቷል። እንደነዚህ ቀለል ያሉ የመገናኛ ዜዴዎች የማህበሩ የአመራር አካላት ከተለያዩ ሰዎች ወቅታዊ አስተያዮቶችን እንዲሰሙ ስለሚረዱ ለማህበሩ ዕድገት ጠቃሚ ናቸዉ ተብሎ ስለሚታመን ወደፊትም ተጠናክረዉ ይቀጥላሉ። ከዚህ ሌላ፣ ማህበሩ አዲስ የFacebook ፔጅ በመክፈት ለማህበሩ አባላት information በተለያየ መልኩ ለማድረስ እየሞከረ ይገኛል። በ2017 በተከፈተዉ የWhatsapp የዉይይት ፎረምም የተለያዩ ወቅታዊ መለክቶችን ለማህበሩ አባላት እያካፈለ ይገኛል። እንዲሁም የማህበሩን ዌብሳይት ከፌደራል መንግስት በተገኘ እርዳታ በማደስ ላይ እንገኛለን። በሚቀጥሉት ትንሽ ወራት የተጀመሩ ስራዎችን በተመሳሳይ ሁኔታ ለመቀጥልና ለመጨረስ ዕቅድ አለ። ከዚህ ሌላ፣ የማህበሩ Bylaw በ2021 እንዲሻሻል ተደርጎ፣ ማህበሩ ሰባት አባላት ባለዉ ቦርድ እንዲመርራ ተደርጓል። ይህም የአሰራር ቅልጥፋና አምጥቷል።

እንግዲህ ባለፉት 40 አመታት ከማህበሩ አቅም አንጻር፣ ቡዙ በጎ ነገሮች የተሰሩ ቢሆንም፣ የተለያዩ ችግሮችም የታዩበት ጊዜ ነበር። በነዚህ ዉጣ ውረዶች ወይም ችግሮች መብዛት የተነሳም ይመስላል፣ ማህበሩ እንደሌሎች ተመሳሳይ ማህበራት መድረስ ከሚገባዉ ደረጃ መድረስ አልቻለም። ለዚህም ዋና ዋና ምክንያቶቹ፣ አንዳንድ አባላት ማህበሩን በፈለጉት መልክ ለማስኬድ ስለሚመኙ፣ ማህበሩን ለራሳቸዉ ጥቅም ብቻ ሲሉ ስለሚቀላቀሉና እንደገቡም እንደማንኛዉም ሰዉ በበጎ አድራጎት ሳይሆን በማወክ ስራ ላይ ስለሚሰማሩ፣ በማህበሩ በኩል የሚገኙ የስፖንሰርሽፕ እድልን ለራስ ብቻ ለማድረግ ስለሚሹ፣ በትክክለኛ ምርጫና በማጆሪቲ ቮት ስለማያምኑና ማህበሩን እኛ ካልመራነዉ ላሳር ስለሚሉ፣ ባጠቃላይ የማህበሩን እድገት ማየት ስለማይፈልጉ ነዉ። ከዚህ ሌላ የማህበሩ አመራር አካላት ምርጫም በትምህርትና በችሎታ የተመረኮዘ ሳይሆን፣ በዕዉቅናና በእንባ ጠባቂነት ላይ የተመሰረት በመሆኑ፣ በዚህ ሁኔታና በጥቂት ሰዎች ጫጫታ መሰረት፣ በርካታ ልምዱና እዉቀቱ ያላቸዉና ለማህበሩ ለመስራት የተዘጋጁ አባላት እንዳይመረጡና እንዳይሰሩ የሚደረጉበት ሁኔታ በተደጋጋሚ ምርጫ በመጣ ቁጥር፣ ሰለሚፈጠር ነዉ። እንደዚህ ከቀጠለም ማህበሩ አደጋ ላይ ሊወድቅ ይችላል።እንደሚታወቀዉ፣ እንደ ካልጋሪ የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ማህበርን ያለን ድርጅት፣ በመንደር ህግ፣ በፖለቲካል ማንፌስቶ ወይም በሀይማኖታዊ ስርዓት መምራት ይከብዳል፤ ህገ ማህበሩም አይፈቅድም። ተደጋግሞ እንደተገለጸዉ፣ የተለያዩ ችግሮች አሉ ከተባለ፣ በውይይት የማይፈታበት ምክንያት የለም። ያለንበት ሀገር በመከባበር ላይ የተመሰረተ ነዉና ጊዜዉም ይኸን ስለሚሻ፣ በመከባበርና በመቻቻል፣ በጋራ ለማህበራችን ለመስራት እንዘጋጅ።

በመጨረሻም፣ እስከአሁን ማህበሩን በፕሬዝዳንትነት በመራሁባቸዉ ግዚያት፣ ከማህበሩ አመራር ጎን በመሆን ለማህበሩ እድገት በጎ ነገር ላደረጉት አባላት በሙሉ ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው። ከዚህ ሌላ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ፣ ማህበሩን ላገለገሉና በማገልገል ላይ ላሉ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴና የቦርድ አመራር ታላቅ ክብር አለኝ። ስራዉ አድካሚ ቢሆንም፣ በአመራር አካላት ብርታትና በአባላት ተሳትፎ፣ እዚህ በመድረሳችን በጣም ደስ ይለኛል። መልካም የ40ኛ አመት ክብረ በዓል ይሁንልን፣ መጭዉ ጊዜ የበለጠ የምንቀራረብበትና አብረን ሰርተን ማህበራችን የምናጥራክርበት፣ የምናሳድግበት፣ ለሀገራችን ኢትዮጳያ አለኝታ የምንሆንበት ጊዜ ይሁን።

ዶ/ር ሉልሰገድ ይማም

The Calgary Ethiopian Community Association (CECA) is a non-profit organization that was established in 1982, and registered in 1983 to provide assistance and support to Ethiopian immigrants. Throughout the past 40 years, the association has grown in steps, flourishing from its humble beginnings, to today's vibrant organization, providing a full spectrum of wrap-around social services, ranging from chances of sponsorship, to employment assistances, skills and training, youth development and a myriad of other support services. In recent years, the association's activities and landscape have widened, involving both old and new, male and female, and young and the most senior members in our community.

One of the main important things that the Association did in the past 40 years is the signing of an agreement with Immigration Refugees and Citizenship Canada (IRCC) to sponsor Ethiopian refugees. In what was considered as our core charitable service, Sponsoring of refugees started in 2000 as a Constituent Group under the Calgary Catholic Immigration Society. In 2002, CECA applied for and obtained a Sponsorship Agreement Holder (SAH) status from Citizenship and Immigration Canada (CIC now IRCC). This agreement was renewed by IRCC in 2018. In 2022, IRCC reviewed the Association's status and strength for sponsoring refugees. Based on the results of this review, the Associations will soon sign a new agreement with IRCC with an approval to continue sponsoring refugees for the next 5 years, until October, 2028.

Apart from the Sponsorship Program, one the major things that was considered as very important achievement by members of the Association and others was the purchase of the Community Center in 2019. The Center has a hall with a capacity of 150 people, a board room, offices, small modern kitchen, in the lower floor, and about 7 offices in the upper floor. The purchase of the center allowed moving the Association's office from a building located in downtown area after 38 years. The purchase of the community center helped the Association attract new members. Currently the Association has over 1900 registered members.

In addition to the purchase of a community center, the Association's leadership tried to help community members during the COVID19 period in 2019-2021. During those years, the Association applied and obtained a grant from the Government of Canada and Canadian Red Cross to address various COVID19 related problems including direct food assistances for those who lost their job because of the pandemic and the mothers who stayed at home to provide care for children. Using the grant, the Association also run COVID19 awareness programs, and provided school supplies to children. In addition, since COVID19 changed the way trainings, presentations, and teaching and learning were given in schools, the Association purchased low cost laptop computers and donated to 40 families. The computer donation helped children in schools and in families living with limited income who otherwise would not be able to access COVID19 resources. By donating laptops, the Association took the initiative to reduce the digital divide immigrants are facing often.

Further, the Association has continued hiring summer students since 2017. The summer student temporarily employment program, funded by the Federal Government, gives unique opportunities for students of Ethiopian decent to get connected with community members and develop their social networks.

Apart from the above activities, the association has continued its participation in the traditional outdoor annual festivals such as the Calgary Stampede. It has also established a Coffee ceremony program where discussions are made on topics important for the community. In an attempt to reach many members, the association has also created a new Facebook account, and improved its website. The WhatsApp Forum that was created in 2017 is now serving as main outlet to share program updates and other important messages with members.

In the next few years, the current leadership will continue to assess the evolving needs of our members. A program for seniors has already been designed and there are also some interest to invest a lot on youth development. As we all try to build the association from down to top, we urge every member to look into his/her own participation. The association's ability to provide services through the past 40 years was only possible through the kindness and generosity of volunteer members and provincial agencies who fund our various programs. As a current president, it is with sincere gratitude and appreciation that I thank members, the leadership, past and present, our frontline volunteers, and our partners and sponsors, for supporting the Association's programs and social activities. Generally, I am privileged to work with a dedicated group of board members and volunteers, who are committed to make the association transparent and free from the influences of political organizations, religious entities, self centered individuals, and crowds. In the past several years, I had the chance to know some of our members, who have stories of their own, some bad and some good. I know where they came from, and what dreams they have. I am honored to be a small part of the help they need, and make their dreams become reality.

As we look forward to the future, we do so with great pride in the legacy of achievement demonstrated by the Association since its inception. At any time, the board members will continue to welcome inputs and new ideas. The leadership is here to represent all members, regardless of race, political affiliation, and religious connections. So don't hesitate to approach us with any concerns or ideas that you may have that can improve community life.

Dr. Lulseged Yimam




Current Board Members: From left to right, Surafel Lakew (Media and Communication), Azeb Mekonnen (Treasurer), Martha Jiru (Secretary), Dr. Lulseged Yimam (President), Nadia Aliyou (Social Affairs), Mahlete Mekonen (Legal Affairs) and Zemene Hailu.




Members of the Exeutive Commiteee (January 2019 to December 2022)



The Inauguration of the New Community Center in 2021



# ከአዘጋጆቹ (Editorial)

ማህበረሰብ በሌለበት ቁሳዊ አለም ውስጥ ታሪክ መኖር አይችልም፣ ቢኖርም እንኳን ታሪኩ ቁሳዊ እንጂ ማህበረሰባዊ አይሆንም፣ ሊሆንም አይችልም።

የተደራጀ ማህበረሰብ ከባርነት ዝማም የወጣ ስለሆነ ሰብዓዊ ትሩፋቱን እውን ለማድረግ ህግንና ሞራልን በመጠበቅ ከቁሳዊ ዓለም ውስጥ የድርሻውን ይሻል። የካልጋሪ የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ማህበር የ40 ዓመት ጉዞም፣ የኢትዮጵያውያን ትሩፋትም ከዚሁ ቁሳዊና ሞራላዊ የህግ ምንጭ የሚመነጭ ስለሆነ ብዙ ተግዳሮቶችንና መሰናክሎችን በማለፍ ለዛሬው ደረጃ በቅቷል። የማህበሩ ጉዞ እንደ ቁጥራችን ባይሆንም፣ ህልውናውን አስጠብቆ ለዚህ መብቃቱ ለቀጣይ ተነሳሺነት ጉልበት ሰጪና አበራታች ነው።

በእድገትም ሆነ በውድቀት ማህበረሰብ በራሱ የሃላፉነት ድርሻ አለው። የካልጋሪ የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ማህበርን ዛሬ ካለበት ወደ ተሻለ ደረጃ ለማሸጋገር ከአባላት የተሻለ ማንም የለም። መደራጀት በሌለበት የእድገት ሂደት እንደሌለ ቢታመንም የሴራ ተግዳሮት የእድገት እንቅፋት ነው። እኛ እትዮጵያውያን ከታሪካችንም ሆነ ከማንነታችን ውህድ የተነሳ ተምሳሌ መሆን የምንችልባቸው ብዙ እሴቶች አሉን። በእጅ የያዙት ወርቅ እንደ መዳብ ይቆጠራል እንደሚባለው እንዳይሆንብን እንጂ እሴቶቻችንን በማክበር ብንተባበር የ40 አመቱን ጉዞ በ4 አመት የእድገት እመርታ መለወጥ እንችላለን። የአለማችን የስልጣኔ እድገት በመተባበር ላይ የተመሰረተ ነው። የተገለለ ማህበረሰብ መኖሩ እንጂ ማደጉ ስለማይታወቅ መብት እድገትና የአስተሰሰብ ስልጣኔ ባለበት ስፍራ እየኖርን ጨለምተኛውን የጉዞ አቅጣጫ መከተል አይኖርብንም። እድገትም ሆነ ውድቀት የአስተሳሰብ አንጓ ስለሆነ ትንሽም ብንሆን ውድቀቱን ንቀን እድገቱን ካነሳን ትልቅ፣ በጣም ትልቅ፣ መሆን እንችላለን።

በመጨረሻም የአገራችን የፖለቲካና ማህበራዊ ህይወት ሁኔታ ሳያውከን፣ ነገሮችን በጥንቃቄ በማየትና ህሊናዊ ፍትህ በመስጠት፣ ከፖለቲካው ውገና ይልቅ የአገርን ህልውና በማስቀደም፣ በእውነት ስርዕት መስራት ይጠበቅብናል። ብሄራችንን ወይንም አለፍ ሲል ደግሞ ሃይማኖታችንን ሳይሆን፣ አገራችንን ወክለን በሌላ ሀገር የምንኖር ዜጎች ነንና ምንጊዜም የትየሌለ አቅማችንን ለአገራችን ሰላምና ልማት ብንጠቀም፣ የህሊናና የሞራል ትርፋማነታችን እጅግ ትልቅ ይሆናል።

**Few Facts about Ethiopia:**

Ethiopia, a nation of rich cultural heritage, stands as one of the world's oldest countries, boasting a recorded history that spans thousands of years, illuminating a captivating tapestry of ancient traditions and civilizations.



alamy.com

The Axum Empire, famed for its towering obelisks, stands among the great civilizations of its time, leaving an enduring legacy through monumental achievements and cultural contributions.




Globalblackhistory.com

The pivotal discovery of "Lucy,"a 3.2 million-year-old hominid fossil, profoundly transformed our comprehension of human evolution and ancestral history.



iho.asu.edu

# ቆይታዬ፣ ከቀድሞ የስራ አመራር

ስሜ ሲሳይ ሙሉአለም ይባላል። በካልጋሪ የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ማህበር በአመራር ለስድስት አመት ተኩል፣ ከ2016 እስከ 2022፣ የህዝብ ግንኙነት ሀላፊ ሆኘ ሰርቻለሁ። በአመራር በቆየሁባቸው ግዜያቶች ያየኋቸውንና የታዘብኳቸዉ ነገሮች ለመጻፍ አጋጣሚ ስላገኘሁ እንደሚከተለዉ አስቀምጨዋለሁ።

የካልጋሪ የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ማህበር፣ ብዙ የመከራ ድልድዮችን አልፏል። በልዩ ልዩ ፈተና ጥሩና መጥፎዉን አሳልፈናል። በዚህ ማህበር ላይ ብዙ በጎ ያልሆኑ ነገሮች ተፈጽመዋል። አሁንም ይህ እንዳይደገም በርትተን ጠንክረን መስራት አለብን።

በማህበሩ ላይ በሚከሰት ነገር ስለተጨቃጨቅንበት፣ ወይም ስለአንተስማማንበት፣ በማዘን ወይንም ማህበሩን ጥሎ መሄድ መፍትሄ አይመጣም። ማህበሩ በህይወት ዘመኑ በሚያሳዝን ሁኔታ፣ ብዙ ፈተናዎች አልፏል። ያን ሁሉ ችግር አልፎ አሁን እየው ለ40ኛ አመት ክብረ በአል ደርሷል፣ ይህ ደስ ይላል።

በካልጋሪ የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ማህበር በአመራር በአገለገልኩባቸዉ ግዜያት፣ ያሳለፍኳችው ፈተናዎችን ለመቋቋም ባልችል ኑሮ ዛሬ በዚህ ጽሁፍ ባልተገናኘን ነበር። ይህ ማህበር፣ በ40 አመት ወስጥ መከራና ግፍ እንደ እዮብ የቀመሰ ነው ብል ስህተት አይሆንም። አንዳንዴ ከህዝብ የሚመጡ ጥያቄዎች ሁሉ መልስ አያገኙም ነበር። ለምን ሲባል፣ የሚመጡት ጥያቄዎች ብዙ ግዜ ቡድናዊ ሆነው፣ ግራ ተጋብተው ግራ ያጋቡ ነበር። በተሳሳተ አስተሳሰብ እና አመለካከት ብቻ በመምጣት እንጂ ለእውነት ለኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ህዝብ የታሰበ ቢሆን እሰይ ብለን እንቀበል ነበረ።

ያላግባብ የሚመጡ ጥያቄዎች ያላግባብ ስምን በማጥፋት ያላግባብ ስምን በጭቃ መለቅለቅ ለማህበሩም ጠቀሜታ ነገር አልነበረውም። ብዙ ነገሮች ታግሰን ስከን ባለ መልኩ በመመልከት ቀኝንም ግራንም በማየት በትግስት በመስራት እየው ዛሬ በተግባር በአይን የሚታየውን አዳራሽ ከመላው ህዝብ ጋር በመተባበር እንዲገዛ ተደርጓል። በዚህም ደስ ይለኛል። ታድያ ይሄን አዳራሽ በማህበሩ ስር እንዳለ ለማስቀጠል፣ ትልቅ አደራ የተጣለበት ደግሞ በካልጋሪ የሚገኘው መላው ኢትዮጵያዊ ነው።

ያሳለፍነው የስራ ጊዜያቶች በመከራ በጭንቀቶች ስናልፍ፣ ልናውቃቸው የሚገቡ እውነቶች አሉ። ታዲያ እውሸት ሲሰለጥን እና ዕውነት ሰትደበቅ አንተ የእውነት ሰው ትሆናለህ ማለት ነው? ያብቻ አይደለም፤ አዛኝ ሆኘ የሌሎች መገፋትን በቀላሉ እንዳይና እንዲሰማኝ አድርጎኛል። ያላግባብ ሲገፉ ያላግባብ ሲነቀፉ፣ የህሊና ቁስል ሲደርስባቸው ኣይተናል፣ አይቻለሁ።

ለብዙ አመታት በማህበሩ አመራር በሰራሁበት ሰአት ያሳለፍኳቸው ችግሮችና ፈተናዎች፣ በህይወት ገጠመኝ ባልማርባቸዉ ኖሮ፣ ዛሬ የተፈራረቁብኝን ፈተናዎች መቋቋም ባልቻልኩ ነበረ። መነቀፍ ምንያህል እንደሚጎዳ ታውቃላችሁ፤ ያም በውሸት። እውቁ የአሜሪካ መሪ ውይም ፕሬዘዳንት የነበሩት ሃሪ ትሩማን ሙቀቱን ከፈራህ ወጥ ቤት አትግባ ሲሉ ተናግረዉ ነበር። ይህን መርህ በመከተል ነበር እኔ ህዝብ የሰጠኝን ሃላፊነት ትቼ አልሄድም በማለት ደከመኝ ሰለቸኝ ሳልል ለስድስት አመት ተኩል ህዝብን ሳገለግል የቆየሁት፣ እንጂ ሙቀቱን ወቀሳውን ሃሜቱን አሉባልታው ወሬው ማህበሩን ለማገልገል የሚገፋፋ አልነበረም።



ሲሳይ ሙሉአለም
Sisay Mulualem

አብረውኝ ከነበሩ የስራ አመራር አባላት፣ ጋር በመከባበር በመተባበር በመደጋገፍ እና በመተሳሰብ የልዩነት ሃሳብን በጠረጴዛ ዙሪያ በመፍታት ለብዙ አመታት አብረን ሰርተናል። በተለይ የሚከተሉትን የአመራር አባላት፣ ሳላመሰግን ባልፍ ንፉግነት ይሆንብኛል። እነዚህ አባላት፣ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ፣

ያማህበሩን አዳራሽ በመግዛታቸው መርጦኝ ባገለገልኩት ማህበረሰብ ስም ምስጋና እቸራችዋለሁ።

- ዶ/ር ልኡል ሰገድ ፡ ፕሬዝዳንት
- ዘመነ ሃይሉ ፡ ምክትል ፕሬዝዳንት
- ማርታ ጂሩ ፡ ጸሃፊ
- አዜብ መኮነን ፡ ገንዘብ ያዥ
- ሃና ገ/መስቀል ፡ ፋይናንስ ክፍል ሀላፊ
- ብርቅነሽ ተክሌ (ውዴ) ፡ የማህበራዊ ጉዳይ
- ሲሳይ ሙሉአለም ፡ የህዝብ ግንኙነት

በአለማችን ሁለት አይነት ሰዎች ይገኛሉ። አንደኛው አናጢና ገንቢ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ነቃፊ ነው። አናጢውና ገንቢው ሁልግዜ አዲስ ነገርን ይፈጥራል፣ ይለውጣል፣ ይጠግናል፣ ያቆነጃል፣ አለም እንደዚህ አይነቱ ሰው ያስፈልጋታል። ለሰው ልጆች እንዲህ አይነት ሰው በረከት ነው። ነቃፊ ደግሞ ሰውበላ ሲሆን በሰዎች ድካም የሚደሰት፣ ፍንጥዝያ የሚያደርግ ነው። ነቃፊ በራሱ ስህተት የተሰራ ሰው ነው። ነቃፊ የሚያወራው በራሱ ድካምና የችሎታ ማነስ ነው።

አንዳንድ ሰዎች ትንሽ ወቀሳ ሲደርስባቸው የሚይዙትን እና የሚጨብጡትን ጠፍቶአቸው ይደነግጣሉ። ለብዙ ጊዜ እህል አልበላ ይላቸዋል። ማሰብ መስራት መተኛት ያቅታቸዋል። ሰው በህይወቱ የወጠነውን ነገር ከግቡ ለማድረስ የሚያስፈልጉትን ነገሮች መካከል አንደኛው ነቀፋ ሲደርስበት የማይደንግጥና የማይደናበር መሆን የኖርበታል። ያላግባብ ስንነቅፍ ያላግባብ ሰዎችን ስለእኛ ክፉ እየተናገሩ ሊያጠቁን ሲሞክሩ፣ ይህ ድክመት እንደሆነ ጠንቅቀን ማዎቅ አለብን።

ታዲያ፣ ከላይ የተጥቀሱት የማህበሩ አመራሮች፣ በዶ/ር ሉልሰገድ ይማም እየተመሩ፣ እሾህ እንቅፋቱን ዳገት ቁንቁለቱን ሃሜቱን ወሬውን ተቋቁመዉ፣ ልዩነታቸዉን አቻችለዉ፣ ታሪክ አንባቢ በቻ ሳይሆን ታሪክ ሰሪ መሆናቸውን አስመስክረዋል። በካልጋሪ ለሚገኘዉ የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ማእከል በመግዛት ከህዝቡ ጋር በመተባበር ትንሿን ኢትዮጵያን መስርተው አሳይተዋል። ለዚህ ማእከል መገዛት መላዉ አባላት ገንዘቡን በማውጣት፣ ሃሳብ በመስጠት፣ ጊዜያቸውን በመክፈል እንዲገዛ አድርገዋል። በመሆኑም፣ ለሁሉም ከፍተኛ ምስጋና አቀርባለሁ። ቸር ይግጠመን።

ሲሳይ ሙሉአለም
ኢትዮጵያ ትቅደም

"The Greatest Glory in Living lies NOT in Never Falling, BUT in Rising Everytime we Fall."

– Nelson Mandela.
South African Former President,
Anti-Apartheid Activist and Politician



Nelson Mandela



# እምቦቀቅላው

የእናቱ መሃጸን ተመችቶት
ዘጠኝ ወር ሙሉ ሞቆት
ቢያላዝን
ቢራገጥ
ቢስቅ፡
ከእምዬ በቀር ማን ሰምቶት
ደሞስ ምን ግድ ብሎት
የራሱ አለም ንብረት ባለቤት
ከእንግዴ ልጅ በቀር ማን ተጋርቶት፡፡
አለሜ ለሁሉም ጊዜ አለው
ያአንተም አለም ከሆዴ ማብቂያው ዘጠኝ ወር ነው
ብላ እናት ና ውጣ
በግድ በውድ አምጣ
ዝርግፍ ወደዝች እራቁት አለም
ወደደም ጠላም
ማለት አይችል መቼም
እምቢ አልወለድም፡፡
እናም ታዲያ የተመቸው ሲፈናቀል
ከሞቀ ቤቱ ዉጣ ሲባል
በዉድ ሳይሆን በግድ ያለፍላጎቱ
በአዋላጅ ተብዬ ክንደ ብርቱ
ተጎትቶ ሲወጣ ሲነቀል ከሞቀ ቤቱ
ከከረመበት ያዉም ከእናቱ፡፡
ኩታዉን ገንጥለው
እንግዴዉን አስጥለው
ከእሚዬ ከዘሩ ያስተሳሰረዉን
ቀርጥፈው ሲጥሉ እንብርቱን
ማነው ያለው ይስቃል?
ያለቅሳል እንጂ ያነባል፡፡
እንቦቀቅላውም ደም ለብሶ ለህጭ ጎርሶ
ሽፉፍኖ ወጥሮ የያዘውን ገርስሶ
ፍትልክ ሲል ደምሥሶ
እንደ ታማኝ ወዳጅ፡
ተቀብላ በተዘረጋ እጅ
አለም ዘቅዝቃ ዉስጥ እግሩን ስትገርፈው
ከእናቱ የጎረሰውን ያን ለሀጭ ስታስተፋው
እሪ አለ ተንጨረጨረ እንቦቀቅላው፡፡
አረ ከቶ ማን ሊሰማው
የአዳም ዘር ዙሪያውን የከበበው
በደስታ እልልታውን አቀለጠው
ለመሆኑ ማን ነው ያለው
የየትኛው ቋንቋ ሊቅ ነው ተርጓሚው
ይሄ ሁሉ መንደርተኛ እልልታውን ያቀለጠው
ስለምን ነው?
ደስ ብሎት እንደመጣ እሚያስመስለው
አረ ጎበዝ ተው!
እስቲ ማን ጠይቆት
ማንስ አባ ከና ብሎት
እንደ እኔ እንደ እኔ ግን ሳስበው
የእሪታ ዋይታ ልቅሶው ትርጓሜው
ያ ሃቀኛው የእውነት ሰው
አቤ ጉበኛው እንዳለው
እንቢ አልወለድም ነው፡
እዉነቴን ነው!!
መወለድ ምን ሊረባው
ላይቡዋርቅ ላይዘልባት ምድር
ለመግባት ለመመዝገብ ከሞት ቁጥር?
ልያዉም ከኛ ካሃበሾቹ ምድር?
አይ አይደለም የሚል ካለ
ሊሞግተኝ የከጀለ
ስማ በሉት ንገሩት
ሰንበት ቀጥሯል እላይኛው ችሎት
ፍርደ ገምድል የሌሌበት፡፡

ስለሺ መኮነን፣ ከካልጋሪ




# የኮሚኒቲ ዕይታ

የኮሚኒቲ ፅንስ ሓሳብ መሰረቱ የማህበረሰብ ውክልና ነው የማህበረሰብ ውክልና ደግሞ አገራዊ ነው። ማህበረሰብ በኑፋቄ አስተሳሰብ ሲጠመድና ጭንጫ አስተሳሰብ ሲነግስ ይበታተንና ውክልና ያጣል። ባለፉት 40 አመታትም የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ብቻ ሳይሆን ብዙ በአልበርታም ይሁን በመላው ካናዳ ያሉ ኮሚኒቲዎች ሲወለዱ ሲያድጉና ሲጎለምሱ ይህንን ውጣ ወረድ አይተዋል። በጦርነትና በሌላም ቀውስ የተነሳ ወይም

የተሻል ኑሮ ፍለጋ ሲባል ህዝቦች ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ይሰደዳሉ ወይንም ይከትማሉ። በአንድ አይነት የጋራ ፍላጎት ላይ የተመሰረቱ ትስስሮች ሲመጡ ማህበራት ይመሰረታሉ። በዚህ አይነት ሂደት የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ተመስርቶ ዛሬ ላለበት ደረጃ ላይ ቢደርስም የእድገታችን ሂደትና ታሪክ ከነባሩ ጋር ሲነፃፀር ትናንት ከተመሰረቱት ማህበራት በልጠን አልታየንም። ሆኖም በየጊዜው በሚመጡ የማህበሩ መሪዎችና በአባላት ጥረት እዚህ ተደርሷል። አሁንም ቢሆን የእንቁራሪት ቁርቁርታና የፌንጣ ሲርሲርታ ሳያውከን እርስ በራስ የምንረዳዳበትን ጎዳናዎች መጥረግ ይጠበቅብናል። እንስሳት መግባባት ስለማይችሉ ይነካከሳሉ፣ ቋንቋ ስለሌላቸው ተወያይተው ወይም ለመወያየት አይደራደሩም። ችግር ካለ አመፀኛ ከመሆን መነጋገር ተሳዳቢ ከመሆን ተናጋሪ ወይም መካሪ በመሆን መጠናከር እንችላለን። ቋንቋዎቻችንና ባህሎቻችንን አክብረንና ተከባበረን ከተገኘን አክባሪዎቻችን ብዙ ይሆናሉ።



ተስፋዬ ቀነኒ
Tesfaye Keneni


እኛው በራሳችን የምንናቆር ከሆንን ንቀትን እንሸለማለን። ለወቀሳ ባይሆንም በኮሚኒቲ ተካሰናል፤ ተሰዳድበናል፤ ተደባድበናል፤ ተኮራርፈናል፤ አሁን ግን ዘመን ተለውጦ እነዚህ የተሸናፊ መዘባበቻዎች ቀርተዋል። በየጊዜው እንዘጭ እንቦጭ እያልን እዚህ ደርሰናል። በተቻለን መጠን ያለንን እያከበርን ለተሻለው እየሰራን ለመገኘት እንሞክር። የተሰሚነት አቅማችን በጥንካሬያችንና ህብረታችን ላይ የተመሰረተ ነው። የዩክሬንን ኮሚኒቲ እንደማያ መውሰድ እንችላለን የፌዴራል መንግስቱ አገራዊና ፓርቲ ዘመም አጀንዳዎች ሲኖሩት የህንድ የቻይና የዩክሬይን ኮሚኒቲዎች የአጀንዳዎቻቸው መገሰቢያ እንዲሆኑ ይደረጋል። በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ሃሳባቸውን እንደ አወዳይ በመነሰነሰ ድጋፍ የማግኚያ መንገድ ያደርጓቸዋል። አይሁዳዊያን የመላውን አለም ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አውታር ተጋሪ መሆን የቻሉትና ለአገራቸው የተሰሚነት ምክንያት የሆኑት መንስዔው የመተሳሰብና የመተሳሰር አንድምታቸው ነው። በውጭ ያለነው ኢትዮጵያውያን፣ ከተባበርን፣ ከተስማምን የአገራችንን ውጥንቅጥ ሁኔታ በአስታራቂነት ወይም በተፅዕኖ ፈጣሪነት ድርሻ ነጣቂ መሆን እንችላለን። ግን እኛ አንድ መሆን ካልቻልን ተፅዕኖ የመፍጠሩን ፊታውራሪነት ላናገኘዉ አንችልም። የህብረታችን ትሩፋት በብዙ ዕሴቶች መገለጥ ስለሚችል፣ የነበርንበትን ትተን ያለንበትን መንደርደሪያ አድርገን ወደ አዲስና ሥልጡን አስተሳሰብ ዘመን፣ እንሻገር።

ተስፋዬ ቀነኒ

"You miss 100% of the shots you don't take."

- Wayne Gretzky
Canadian Hockey Player





# የማህበራዊ ሚድያ ተፅዕኖ

አባት:-" ኧረ ተው ልጄ፤ ፌስቡክ አጠቃቀምህ ልክ ይኑረው!"
ልጅ:-" አባየ "ኮሜንትህን" ተቀብያለሁ። ግን ሁሌም "ኦንላይን" መሆኔ ምን ችግር አለው?"
አባት:-"ችግር አለው እንጅ! ፌስቡክ ላይ ከማዘውተርህ የተነሳ ባህል ወጋችን ዘነጋህው እኮ።"
ልጅ:-"አትሳሳት አባየ ስለ ባህል ወጋችን ጠንቅቄ አውቃለሁ።"
አባት:-" እስኪ እንደው በሞቴ በባህላችን መሰረት በአውዳመት ጊዜ የበግ አተራረድ ስርአታችን ምን እንደሚመስል ከመጀመሪያው ጀምሮ ንገረኝ?"
ልጅ:-"መጀመሪያ ገበያ ወጥተህ በግ "ሰርች" ታደርጋለህ።"
አባት:-" በግ ትፈልጋለህ ማለትህ ነው? እሽ ከዛስ?"
ልጅ: " ከዛ በጉን ቤት ታመጣና መሬት ላይ "ዳውንሎድ" ታደርገዋለህ።"
አባት:-" መሬት ላይ ትጥለዋለህ ማለትህ ነው? እሽ ከዛስ?"
ልጅ:-" ከዛማ አንገቱን "ሾርትከት" ካደረክ በኋላ ቆዳውን "ሪሙቭ" ታደርገዋለህ።"
አባት:-"ወቸ ጉድ! ከባረከው በኋላ ቆዳውን ትገፋለህ ማለትህ ነው? ሆሆ! ከዛስ?"
ልጅ:-"ከዛ በኋላ ሆዱን "ኦፐን" ታደርግና ሆዱ ውስጥ ያሉ "አፕሊኬሽኖች" ታወጣለህ።"
አባት:- ጉድ ነው! እሽ ከዛስ?"
ልጅ:-" በመጨረሻ "አፕሊኬሽኖችን" ታወጣና "ፎልደር" ላይ ማስቀመጥ ነው።"
አባት:-"ስጋው ሰሃን ላይ ታስቀምጠዋለህ ማለትህ ነው ኪኪኪኪ... ከዛስ?"
ልጅ:-" በመጨረሻም "ላይክ" ያደረግነውን የስጋ አይነት ወደ ሆዳችን "መፖስት" ነው።

.

አባት:-" አንድ ነገር ረስተሃል ልጄ..ጎረቤቶቻችን "ሼር" እንዲያደርጉ "ኢንቫይት" ማድረግ አለብን!"

Source: https://habeshajokes.blogspot.com/2018/03/blog-post.html

********************************

ባል ለሽንቱ ወጣ እንዳለ ሚስት ስልኩን አንስታ ቴሌግራም ላይ ስትገባ ከብዙ ሴቶች ጋር ተጻጻጽፏል አንድ በአንድ ማንበብ ትጀምራለች
እሳት ለብሳ እሳት ጎርሳ እቤት እስከሚገባ ንዴቷ አላቻል ብሏት ስትንቆራጠጥ
ባል ደረቱን ነፍቶ እንደገባ
ሚስት:-እሺ የኛ ታማኝ
ባል:-ምነው ማሬ
ሚስት:-ጉድህን እኮ አየሁልክ ከኔ ሌላ ሴት በስልክ እንደምትጻጻፍ እንደምትጀናጀን ደርሼበታለሁ

.

ባል:-ማ እኔ ማር አረ በፍጹም የምን መጻጻፍ
ሚስት:-ስልኩን ብድግ አርጋ ይሄ አንተ አይደለክም ምን ማስረጃ ፈለክ ከዚ ሌላ

ባል በዚ ጊዜ ምን ቢል ጥሩ ነው
አረ ይሄ የኔ የእጅ ጹሁፍ አይደለም
******************************************

ባል ለሚስት በቴክስት "ነገ ለስብሰባ ወደ ክፍለ ሃገር ስለምሄድ ከውስጥ የምለብሳቸውን ልብሶች ቅያሬ እና ሸሚዝ እንዲሁም ካልሲ በሻንጣ አዘጋጂልኝ።"

ትንሽ ቆይቶ እንደገና ሌላ መልዕክት "ውይ ሳልነግርሽ እረስቼው: ባለፈው የተወዳደርኩበት ቦታ እኮ አለፍኩ፣ የደስ ደስ ያንን የእራት ቀሚስ ገዝቼልሽ እመጣለሁ፤"

ሚስት በቴክስት፣ "አረ: እስቲ ሙች በለኝ?"
ባል ከእንደገና በቴክስት: "አረ ውሸቴን ነው፣ የመጀመሪያውን መልዕክት እንዳየሽዉ ለማወቅ ነው።"

************************************

ፍቅረኛውን ደውሎ እያናገራት ነው
ወንዱ:- ፍቅሬ
ሴቷ:- አቤት ማሬ
ወንዱ:- ለኔ ያለሽን ፍቅር በአንድ ነገር ግለጪ ብትባይ በምን ትገልጪዋለሽ
ሴቷ:- እንዴ ማሬ፣ እኔ ላንተ ያለኝን ፍቅር ሊገልፅ የሚችል አንዳችም ነገር በአለም ያለ አይመስለኝም፣
ወንዱ:- እንደው ሞክሪ ብትባይስ
ሴቷ:- እሺ በቃ እኔ የሞባይል ቀፎ ነኝ አንተ ደግሞ ሲም ካርድ ነህ ቀፎ ያለ ሲም ባዶ እንደሆነ ሁሉ እኔም ያለ አንተ ባዶ ነኝ፣
ወንዱ:- በጣም ነው የምወድሽ ብሎ ስልኩ ተዘጋ፤
ሴቷም ወደ ሰማይ ቀና ብላ ተመስገን አምላኬ እንኳዋን ባለ ስንት ሲም ቀፎ እንደሆንኩ አላወቀ አለች ይባላል።



የልጆች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት



Community Dialog in the Association's Community Center




Members of the Association ready to Particpate in Calgary Stampede - 2019



# እናንተ እኔን ብትሆኑ?

ስማ አለኝ አለቃዬ ስሜን ተጣርቶ። ስማ ትናንት እኮ ያ የምወደውን የእናንተን ባሕላዊ ምግብ ከቤተሰቦቼ ጋር ሆነን በላን። ምንድን ነበር ስሙ አለኝ ለማስታወስ እየሞከረ ፣እኔም የትኛውን እንደሚለኝ ስለገባኝ ኦ ዶሮወጥ ነው? ሁሌ ስነግርህ አልያዝከውም፣ እስቲ ዶሮ ወጥ በእንጀራ ደጋግመህ በል አልኩት፣ደጋግሞ ሞከረ፣ ድሮ ወት ቤንጀራ፣ አይደለም ዶሮ ወጥ በእንጀራ በል እያልኩ እንዲዪዘው አስለፈለፍኩት። ይህ ሰው ስሙ ኦዚ ይባላል በአባቱ የላቲን ወገን ሲኖርበት በእናቱ ካናዳዊ ነጭ ብለን በተለምዶ እንደምንለው የሁለት ዝርያ ውጤት ነው። እንግሊዝኛ ቋንቋው ቢሆንም ላቲንኛ ይናገራል ይሰማል። ጥሎበት ኢትዮጵያን ይወዳል ብሎም ኢትዮጵያዊ ሲያገኝ ለመቅረብ ለማነጋገር ይጥራል፣ ምክንያቶቹንም ሲያነሳ ባሳለፈው በዩኒቨርስቲ የትምህርት ጊዜው የታሪክ ሳብጀክት ሲማር ኢትዮጵያ በጣልያን በተወረረች ጊዜ በወቅቱ የነበሩት የተባበሩት መንግስታት ሀገሮች ለጣልያን ሲያብሩ የአሁኗ ሜክሲኮ የአባቱ አገር ከኢትዮጵያ ጋር ቆማ እንደነበረና የኢትዮጵያ ሕዝብ ምንያህል መስዋእትነት እንደከፈለ መማሩን የሚያስታውስ ሲሆን በዚህም የተነሳ በጣም ነው የማደንቃችሁ ብሎ አጫውቶኛል። በተጨማሪ አባቱ ስለ አለም ታሪክ ሲያጫውቱት ስለ ኢትዮጵያ ብዙ እንዳስረዱት ነግሮኛል። ኦዚ መጠርያ ስሙ ቢሆንም እኛ የስራ ባልደረቦቹ ግን አሚጎ ብለን እንጠራዋለን።

አሚጎ እንደውም አንድ ጊዜ ያለኝን አልረሳውም፣ እኔ አለ፣ እኔ የአሁኗ ባለቤቴ ከወጣትነታችን ጀምሮ በፍቅር ከንፋ ሙጭጭ ብላብኝ ነው እንጂ ኢትዮጵያዊ ሴት ነበር የማገባው አለኝ፣ እንዴት ብዬ ስለው በቃ ቆንጆ ናቸው ብሎ አሳቀኝ። አሚጎ በስራ ድርሻው ጥሩ ቦታ ላይ ቢሆንም እንደ አለቃ እዩኝ አይልም። የሁለት ውጤት በመሆኑ ይሆናል ዘለግ ያለ በጣም ያልነጣና ጉንጩ ላይ ሰርጎድ ያለች ዲምፕል ያለው ፈገግታ የተላበሰ ጎልማሳ የማይከብድ ቀለል ያለ ሰው ነው። አጋጣሚ ሊሆን ይችላል ባለቤቱም እንደሱ ዘለግ ያለች ትህትናና ፈገግታ የተላበሰች ናት። ለመጀመርያ ጊዜ ያየኋት የካምፓኒያችን እድሜና የተመሰረተበትን የአርባኛ አመታት አከባበር ላይ ቤተሰቦቻችን በተጋበዙበት ዝግጅት ላይ ነበር። በጣም እንደምትወደው ያስታውቅባታል የቀኝ እጇን በግራ እጁ መሀል ልካ ምግብ ለመመገብ ካላወጣችው በስተቀር ሶቶ አግብታ ፕሮግራሙ እስካለቀ ድረስ ጭምቅ ነው፣ ይሳሳቃሉ ይጫወታሉ ያጫውታሉ። በሕይወት ጉዞ ውስጥ ሙሉ የማያደርጉ ብዙ እንከኖች እንዳሉ ሁሉ እነ አሚጎም ቤት የልጅ አለ ማግኘት አለመፈጠር ቢኖርም እነሱ ሌላ ማህበረሰብ ናቸውና ፍቅራቸውን አልፈተነውም።

ለእዚህ ጽሑፍ መነሻ የሆነኝ ቁምነገር ሊከሰት የቻለው አልፎ አልፎ፣ ትናንት የእናንተን የምወደውን ምግብ በላሁ ይለኛል። የትኛው ምግብ ቤት ወይም (restaurant) ሄደህ ነው እያልኩ ስጠይቀው፣ አልነግርህም ይለኝና ይቀልድብኛል። በተለይም ባለቤቱ ከዶሮው ጋ ተቀቅሎ የሚመጣውን እንቁላል ብቻውን አላምጣ ስትውጠው አይ ላቭ ዚስ ፓርት ( I love this part) የምትለው ነገር እንደሚያስቀው ስቆ ይነግረኛል። ነገሩ ወዲህ ነው፣ ኦዚ ወይም አሚጎ ጥሩ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኝ ሲሆን ባለቤቱም የተማረች የተመራመረች በአንድ የነዳጅ ማውጫ ኩባንያ ውስጥ በኬሚስትሪ ዲፓርትመንት እንደ ሀላፊነት ቦታ ላይ ያለች እንደሆነ ተረድቻለሁ። ስለሆነም ጥሩ ገቢ ያላቸው፣ የሚኖሩበት ቤት በቀላል ዋጋ የማይገመት አካባቢያቸው ያሉት መኖርያ ቤቶች በከተማው ውድ የሆኑ፣ የተገነቡበት ማቴርያልስ ወይም የግንባታ ቁሶች ውብ የሆኑ ከነዋሪው ውጪ ሌላ ሰው ዝር የማይልበት ሲሆን እያንዳንዱ ግቢ የራሱ የሆነ የቴክኖሎጂ መቆጣጠሪያ የተገጠመለት በተጨማሪም በተሽከርካሪ ውስጥ ሆነው ዙሪያውን የሚቃኙ የደህንነት ተቆጣጣሪ ባለሙያዎች የሚመደቡበት አካባቢ ነው። እዚህ ነው እንግዲህ ኦዚና ባለቤቱ ኑሯቸውን ያደረጉት።

በካልጋሪ አንድ ቆንጆ ጸሀያማ የበጋ ወራት ቀን በመስሪያ ቤታችን የሻይ ሰአት ውጭ ቁጭ ባልንበት ኦዚ እንዲህ አጫወተኝ። በመኖሪያ ቤቱ አጠገብ አንዱ ጎረቤቱ በጣም ጥሩ ቤተሰቦች የሆኑ እንዳሉ እነዚህ ሰዎች ሁሌ ድግስ እንደሚያደርጉና ቤታቸው በብዙ ሰው እንደሚሞላ መኪናዎቻቸው በጣም በውድ ዋጋ የሚገዙ፣ ልጆቻቸው ውድ በሆኑ እውቅና ባላቸው ትምህርት ቤቶች ውስጥ እንደሚማሩ፣ ለእረፍት የሚሄዱባቸው አገሮች በጣም ብዙ ዶላር የሚያስፈልጋቸው፣ ግን ምን እንደሚሰሩ ወይም የገቢ ምንጫቸው ከምን እንደሆነ እንደማያውቅ አጫወተኝ

እኔም በዛ ቅጽበት ወደ እራሴ ለእራሴ ታድያ እዚህ አገር እኮ ሀብታሙ ብዙ ነው ሀብቱ የግለሰቦች ነው ይህ የሚነግረኝ ጎረቤቱ የአንድ ካምፓኒ ባለቤት ሊሆን ይችላል ምን ያስደንቃል ብሎ ነው የሚነግረኝ ብዬ ከእራሴ ጋ ሳወራ፣ ምናልባት እኮ ታውቃቸው ይሆናል ብሎ ሲያናግረኝ፣ እንደመባነን ብዬ እንዴ እኔ ደሞ

በምን ያገናኘናል ብዬ ስስቅበት፣ ሰዎቹ እኮ የአገርህ ሰዎች ናቸው። ትላንትና ዶሮ ወጥ በላን እያልኩ የምነግርህ እነዚህ ኢትዮጵያዊያኖች ቤት ነው አንዳንዴ ዝግጅት ሲያደርጉ ይጠሩናል ሲለኝ ያላሰብኩትና ያልገመትኩት አጋጣሚ ስለሆነብኝ እየሳኩ ምግብ ቤቱን አልነግርህም ያልከኝ ለእዚህ ነው ብዬው እየተሳሳቅን የዕረፍታችን ሰአት በማለቁ ወደ ውስጥ ተመለስን። በሚቀጥሉት የተለያዩ ቀኖች ኦዚ ስለነዚህ ኢትዮጵያውያን ጎረቤቶቹ ያየውን ያጫውተኛል።

አንድ ጊዜ ሌተስት መኪናዎቻቸውን በሌተስት መኪና ቀየሩ ይለኛል፣ ሌላ ጊዜ አንድ ወር ሙሉ እቤት አልነበሩም ይለኛል፣ ሰንብቶ የጊቤአቸውን ደህናውን አስፋልት መንገድ አስልጠው እንደ አዲስ ያሰሩታል ይለኛል፣ ዝግጅት አድርገው ጠርተውን የሆነ ስትሪት ሕንጻ ገዛን አሉ ብሎ ይነግረኛል፣ እነዚህ ሰዎች የሌላ ዜግነት ያላቸው ሊሆኑ ይችላሉ ብዬ እንዳልጠራጠር ዶሮ ወጥ ያበሉናል ብሎኛል ብቻ በብዙ መንገድ ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን በደንብ አሳምኖኛል።

ከጊዜ ወደ ጊዜ ነገሩም እየከነከነኝ መጣ፣ እነዚህን ሰዎችም ማየት አለብኝ ብዬ ወሰንኩ እንዲያሳየኝም ኦዚን መወትወት ጀመርኩ። አሚጎ (ኦዚ) ከመግባባታችን የተነሳ ሊያሳየኝ እቅድ ነደፈ፣ እንዲህም አደረገ። አንድ እሁድ በመኪናው ወስዶ ከኋላ እንድቀመጥ አደረገኝ፣ ግቢው በር ላይ እኔን ውስጥ ትቶ ከውጭ አቁሞ የጊቢውን በር ሙሉ ለሙሉ ከፈተው፣ ፕላስቲክ ቱቦ የጊቢ ሳር ማጠጫ በረጅሙ ይተረትር ጀመር። ያን ቀጭን ፕላስቲክ ቱቦ ወደ ውጭ ካለው የአጥሩ ስር ሳርና አበቦች ወደ በቀሉበት አመጣውና መሬቱ ላይ አስቀምጦ እኔ ወደ አለሁበት መኪና ውስጥ ገባና ወረቀት እንደሚፈልግ አስመስሎ እንዲህ አለኝ፣ በማንኛውም ደቂቃ ሰውየው ከጊቢው ይወጣል እኔን ሲያይ ሰላም ለማለት ወደእኔ ይመጣል አንተ በዛ ጊዜ ምንም ሳትንቀሳቀስ በደንብ ለማየት ትችላለህ ብሎኝ አትክልቶቹን ውሀ ሊያጠጣ ሄደ አንድ ደቂቃ አለፈ፣ አስር ደቂቃ፣ አስራ አምስት፣ ሰአቴንና፣ ኦዚን የምጠብቀውን ተናፋቂ በር በር አያለሁ። መሬቱ ውሃው መፍሰሱ በዝቶበት መልሶ ይተፋዋል አፈሩ አብሮ ከውሀው ጋ ሄዶ እንዳያልቅ ፈራሁ። ይሄ ሰው እኔን ለማስደሰት ብሎ አበቦቹን ሊያጣ ነው እያልኩ እራሴን ስወቅስ፣ ከኦዚ የሚቀጥለው የጎረቤቱ ሸንጣሙ የጊቢ በር እራሱን በእራሱ እያዘዘ እየኮራ ወደ እዚህም ወደ እዛ እንደ እባብ እየተሳበ ለሁለት ሲከፈል አንድ ብርማ ቀለም አዲሱ ሞዴል ቴስላ መኪና ብቅ አለ። ወድያውም ቆም በማለት ዝቅ  በሚል የመስተዋት መስኮት ውስጥ ሀይ ኦዚ ባይ ኦዚ የሚል ድምጽ እንደ ሰማሁ የኦዚ እጅ ሲውለበለብና መኪናው ሲከንፍ አንድ ሆነ። በግምት የሰውየው ትልቁ ልጁ ሳትሆን አትቀርም ብዬ ገመትኩ። ከደቂቃዎች በኋላም ያ የሚንጎማለለው በር እንደለመደው ተዘግቶ እንደተለመደው ተከፈተ አሁን ሰውየው ነዉ ብዬ ስል በጣም ከቀላ የቮልቮ ሞዴል መኪና ውስጥ  የአዋቂ የሴት ድምጽ የመሰለ ሰላምታ አሰጣጧም በዝግታ አነዳድ ጊዜ የወሰደ ሲሆን የሰውየው ባለቤት ናት ብዬ ብገምትም ያደረገችው ፊት ሙሉ የሚሸፍን መነጽር ግምቴን ሙሉ አላደረገውም፣ ሴትዬዋ በዝግታ አነዳድም ከአይን ተሰወረች። በእዚህ መሀል ኦዚ እርጋታው እንዳለ ነው የእኔ ፍራቻ አበባዎቹ በውሀው ብዛት ተነቃቅለው እንዳይሄዱ ነው። እኔ የዛሬ እድል እንዳያመልጠኝ የግቢውን በር በሩን አፍጥጬ እያየሁ እፀልያለሁ፣ ኦዚ ውሀውን ያንዠቀዠቀዋል። አቤት እዚህ አገር በፈሰሰው ልክ ስለሚያስከፍሉ የሚቀጥለው የኦዚ ቢል እጥፍ ባይመጣ ነው እያልኩ ሳስብ ያ ህይወት ያለው የግቢው በር ለሶስተኛ ጊዜ ድምጽ እንደሌለው ወንዝ መሰስ እያለ ሲከፈት ሞዴሉ ማርቸዲስ ከለሩ ነጭ የሆነ መኪና ከግቢው ወጣ እንዳለ ቆመ። ወድያውም የመኪናው በር ተከፈተና አንድ በሙሉ ልብስ ዝንጥ ያለ፣ ጫማው የሚያብረቀርቅ፣ ቁመቱ ከኦዚ ጋር የሚስተካከል ጠየም ያለ ሰው ወጣና ወደ ኦዚ ለሰላምታ እየተራመደ መጣ። ይህ ሰው እሱ አያየኝም እኔ ግን በደንብ ላየው በምችልበት ቅርበት እንዳለሁ የሚያውቀው ነገር የለም። ወድያው ሰውየውን እንዳየሁትም ሳልስበው ልጮህ ነበር። ከመቅጽበትም አፌን በእጄ አፍኜ እራሴን ተቆጣጠርኩት። ሰውየውን ለረዥም ጊዜ ባላየውም በፍጹም ገጹ አይጠፋኝም እሱ አያውቀኝም እኔ ግን አውቀዋለሁ የኢትዮጵያ ሕዝብም ያውቀዋል ለማንም ሊጠፋ አይችልም እሱም እራሱን ለመደበቅ ምንም የተጠቀመው ማደናገሪያ የለም። ለነገሩ ያለበት አገር የሰው ልጅ ጫፉ የማይነካበት ቀና ተብሎ የማይታይበት የህግ አገር ነው ያለው ማንን ፈርቶ ይደበቃል አልኩ ለእራሴ። ያኔ በቴሌቪዥን ከማየው በላይ አምሮበታል የደላው ሰውነቱ ይናገራል። በስልጣኑ ተጠቅሞ የኢትዮጵያን ሀብት አሸሽቶ እዚህ የምድር ገነት ኑሮውን ከቤተሰቦቹ ጋር ያጣጥማል ማንነቱን አልነግራችሁም ይህ ሰው ከደርጉ ባለስልጣን አንዱ ሊሆን ይችላል ከዛም በኋላ ከነበሩት ውስጥ ሊሆን ይችላል ከአሁኖቹም ባለስልጣናት አንዱ ሊሆን ይችላል። ይህ ሰው ቤቱ ውስጥ ያለውን ቁሳቁስ አይቼ ለመገመት ባልችልም ግቢው ከእነ መዋኛው የተንጣለለውን ርስት በጋሻ ይህን ያህል ማለት ባልችልም፣ እንደው በሚገባን መልኩ ሀብቱን ገምትልን ካላችሁኝ፣ ባንክ ሊኖረው ይችላል ብዬ

የምጠነቁለውን ዶላር አስቤ ያየሁትንና የሰማሁትን ንብረቶች ደማምሬ በቃ እርፍ በሉት አንድ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ይገነባል ብዬ በቀላሉ ላረጋጋችሁ።

ይህ ሰው የድሀ ደም አሻግሯል፣ ሳይማር ያስተማረውን ሕዝብ ሐብት ይዞ ኮብልሷል፣ ብዙ ትምህርት ቤቶች በኪሱ ይዞ እፍ እልም ብሏል፣ ኪሊኒኮች ይዞ ተሰውሯል፣ የውሀ ልማቶች ጭልጥ አድርጎ ጠጥቷቸዋል፣ በቀላል ማስረጃ ብገልጸው ሊገባችሁ ይችላል ብዬ እናንተን የማስረዳ መስሎኝ በመንፈስ ጭልጥ እንዳልኩ ኦዚ መኪናውን ከፍቶ እስኪገባ እኔ እዛ አልነበርኩም። ሰውየውም ከኦዚ ጋር የሚያወራውን አውርቶ በቆርቆሮው ከቤቱ እርቋል። ኦዚም ሳቅ እያለ ታውቀዋለህ በደንብ አየኸው አይደል? ብሎ ሲጠይቀኝ ብዙ ሀሳብ ተመላለሰብኝ። አዎ በደንብ አይቸዋለሁ አልኩት ግን ከእናንተ ከአንባቢዎቼ ጋር እስከመካከር ምን ልበለው ብዬ ከእራሴ ጋር ሙግት ገባሁ። የህዝብ ደም መጣጭ ነው ልበለው? በአገሬ ተፈላጊ ሰው ነው ብዬ ልንገረው? ሆስፒታል፣ ትምህርት ቤት፣ መንገዶች፣ የፋክተሪዎች ዋጋ፣ የውሀ ፕሮጀክቶች ብር መንዝሮ መጥቷል ልበለው፣ ወይም ምንም አዲስ ነገር ላይመጣ ጉርብትናቸውን አልረብሽ? አልንገረው ሲጋበዝ ይሂድ የሚወደውን ድሮ ወት ይብላ፤ እናንተ እኔን ብትሆኑ ምን ታደርጋላችሁ?

አፈወርቅ ገብረሚካኤል፣ ከካልጋሪ

# Interview with Dr. Alula Damte, Former President of the Association

**ጥያቄ - በምን ሃላፊነት ቦታ ሰርተሀል? ጊዜው?**

I had the pleasure of serving the Calgary Ethiopian Community Association as the President from 1998-2004 and as the Chairman of the Board from 2004-2008.

**ጥያቄ - ያጋጠመህ ተግዳሮት ነበር ወይ?**

Like the city it resides in, the Calgary Ethiopian Community Association has gone through major cycles of boom and bust. When we joined in 1998 , it was on life support hanging on for dear life. The challenge that was presented to us was to revive the association and find a way for it to grow in a sustainable manner avoiding or minimizing the frequent downturns that threatened its very existence. In addition and on a more practical level, maintaining neutrality during a divisive period be it due to religion/church and/or political/ethnic affiliation required a very careful stick handling.



Dr. Alula Damte

**ጥያቄ - ማህበረሰቡ ወደ ኮሚኒቲው እንዲመጣ ምን መደረግ አለበት ትላለህ?**

To answer this question, one needs to understand who the target demography is. It is the first arrivals who came over in more or less steady stream over the past 40 years (or even longer considering there were people from Ethiopia pre 1983). It also includes their children and grand children who have assimilated and called Canada/Calgary their home.

So, I believe the answer lies in the recognition that we live in a transactional world and simply being of Ethiopian origin is not sufficient to attract wider membership. Members need to see and get tangible benefits from the association similar to the ongoing sponsorship, advocacy, language school etc, programs. The newer "Edir" type initiative is reflective of current needs and how community association can help and expand its membership. There has been attempts to reach out to the second/third generation but their needs are very different from the needs of the first arrivals. In fact, I would venture to say there is a major lack of appreciation of the issues they face in their day to day lives. Using the organizational capacity resident in the association, outreach to this sector is very important and ensures the longevity and expands the relevance of the community association.

**ጥያቄ - የምትኮረበት ወይም የምትፀፀትበት ነገር አለ ወይ?**

Among the many things that I am proud we achieved, a few of the highlights include; managing a non-catastrophic transition of power after our term was up with capital in the bank and a much healthier active membership count; welcoming the fist person to Calgary who came through our refugee sponsorship process; receiving several heads of states from Africa and the Secretary General of the UN during the G8 Summit representing Ethiopians in Calgary.

One always regrets missed opportunities to do more. I felt we spent far too much energy re-building the community that could have been spent on initiating more programs that would have benefited the members. The Executive team that was put together at the time were professionals with capacity to do a lot more had we not spent so much effort just to build consensus and neutrality.

**ጥያቄ - የአርባኛ አመት በአሉን አስመልክቶ ለአንባቢዎቻችን የምታስተላልፈው መልዕክት ካለ? What do you think for the future about the community?**

The community association has been around for 40 years. The early settlers are now parents and grandparents whose needs are very different from either the kids born here or the younger first arrival crowd. There are people here from the time of teklay Gizat to Killil, and even through the change of the political boundary of the country. People have sung national anthems ranging from the imperial Ityoṗya hoy des ybelish, the revolutionary Ityopp'ya, Ityopp'ya, Ityopp'ya qedämi, and the Wedefit Gesgeshi Widd Innat Ittyoppya.

Needs are complex and ever changing which requires great flexibility and foresight. We need to understand and adapt, issues of yesteryears are no longer the same or relevant. The community should expand its services to find a way to involve the ones born here. They are old enough to identify issues they need help with and design a solution, let's give them a platform. I see bright future ahead for the association, and I truly believe it is as its strongest point than it has ever been. It has the means and capacity to launch programs that would have lasting impact on the membership at large.

Congratulations for making it this far and hope for many more great years ahead.




ካልጋሪ የኢትዮጵያ ኮምዩኒቲ
CALGARY ETHIOPIAN COMMUNITY



Some of the  Assocation's Coffee Cermonies




# “አሁን ለምንድነው ፈሪ ማቀንቀኑ ቅጠል አይበጠስ ካልደረሰ ቀኑ!”

ከዕለታት አንድ ቀን ልክ እንደ ደራሲ ስብሐት ልብ ወለድ ባሕሪ፤ እንደ አጋፋሪ እንደሻው፤ ሞትን የሚፈሩና የሚሸሹ አቶ መርኔ የሚባሉ ባላባት ነበሩ። የሰፈሩ ሰው አብዬ መርኔ እያለ ነው የሚጠራቸው።

አቶ መርኔ ሞትን ለማሸነፍ ሲሉ ወደፊት የሚሆነውን ነገር የሚተነብዩ ኮከብ ቆጣሪዎች ዘንድ ሄደው ኮከባቸውን አስቆጥረዋል፣ የወደፊታቸው ሁኔታ፣ ፍፃሜያቸው ምን እንደሚሆን ለማወቅ ከጅለው የመዳፍን መስመር እያዩ የሰውን የወደፊት ዕጣ ፈንታ የሚናገሩ መዳፍ አንባቢዎች ዘንድም ሄደዋል፣ ዕጣዬን እዩልኝ ብለው የተለያዩ አዋቂዎችን ጠይቀው አስነብበዋል። ሞራ ገላጮች የሚባሉ የሰው መፃዒ ዕድል ተናጋሪዎችም ጋ ሄደው የወደፊት ፍፃሜ ሕይወታቸውን ለማረጋገጥ ሞክረዋል። የቡና ስኒ አይተው ስለ ዕድል የሚናገሩ ሰዎች ቤትም ሄደው “መጨረሻዬን ንገሩኝ እባካችሁ?” ብለው ተማጥነዋል። በየመፅሐፍ - ገላጩ ሰፈር እየዞሩ የነገ ሕይወታቸውን አላፊ ዕድሜ ሊያስጠኑ ጥረት አድርገዋል። አብዬ መርኔ ያልሄዱበት ቦታ የለም።

ሁሉም አዋቂዎች የሚሞቱባትን ሣምንት ጠቅሰው፣ ”የፈለጉትን ጥንቃቄ ቢያደርጉም፤ የሚሞቱት በእሾህ ተወግተው ነው!” ሲሉ ነገሩዋቸው።

አብዬ መርኔም በልባቸው፤ “እንዲያማ ከሆነ እኔ እሾክ የደረሰበት አልደርስም! እንዲያውም ከእነአካቴው ከቤቴ አልወጣም” ይሉና በነዚያ በተጠቀሱት ቀናት እቤታቸው ክትት ብለው ሰነበቱ። ከተባሉት አንድ ቀን ብቻ ነው የቀራቸው። ቤታቸው በረንዳ ላይ ተቀምጠው አላፊ አግዳሚውን የሰፈራቸውን ሰው ሰላም እያሉ፣ “እንዴት ሰነበትክ ?” ሲሉ አመሹ። ወደ ቤታቸው ሊገቡ ጥቂት ሲቀራቸው፣ የከብት እረኛቸው፣ ላሞችና በጎች እየነዳ መጣ። አብዬ መርኔ ከግልገልነቱ ጀምሮ ያሳደጉትን በግ አዩ፡፡ በጣም ደስ አላቸው። በጉ ያውቃቸዋልና እየሮጠ ወደሳቸው መጣ። እያሻሹ ሲያጫውቱት ድንገት በፀጉራም ቆዳው ውስጥ የነበረ አንድ እሾክ መዳፋቸውን ጠቅ አደረጋቸው! ደማቸው ከፉኛ ፈሰሰ። ቁስሉ ተባባሰና አልሽር አለ። ለካ ያ እሾክ መርዝነት ኖሮት፣ ብዙም ሳይቆዩ ለሞት አበቃቸው!




**Did you know?** The DNA is stored into a microscopic nucleus but can be stretched to 6 feet in length



DNA Illustration

DNA, or deoxyribonucleic acid, is a molecule that stores genetic information in living things. It looks like a twisted ladder and is made up of four building blocks: adenine (A), thymine (T), cytosine (C), and guanine (G). These blocks are arranged in a specific order, forming a code that guides an organism's growth and functions. DNA replicates before cells divide, ensuring the new cells have the same information. Genes, segments of DNA, contain instructions for making proteins that perform vital tasks in the body. Variations in DNA sequences lead to differences among individuals and species, playing a role in traits, diseases, and evolution. DNA analysis is used in forensics and helps us understand the diversity of life on Earth.

“ዓለም አላፊ ነው መልክ ረጋፊ ነው፣ ፎቶግራፍ ቀሪ ነው!” ይላሉ የጥንት ሰዎች። ከተፃፈልን ቀን አናልፍም። የዕጣ-ፈንታችን ነገር ነው። በሕይወት የምንኖርባትን እያንዳንዷን ደቂቃ እንጠቀምባት እንጂ ነገን አንጠብቅ። በእጃችን ያለውን ወርቅ ቀን ሳንውል ሳናድር ጥቅም ላይ እናውለው።

ሀገራችን የጦር አውድማ ከሆነች አያሌ ዓመታት ተቆጥረዋል። ስደት እንደ አዘቦት ቀን ልብስ ከተዘወተረ ከራርሟል። መፈናቀልና ቀዬን ለቅቆ መሄድ ወረት መሆን ከተወ ቆይቷል። ይሄም ያልፋል እያሉ እጅን አጣጥፎ መቀመጥ ሞኝነት ሆኗል። መንግሥትም፤ “የበላችው አቅሯታል፣ በላይ በላዩ ያጎርሳታል!” እንደሚባለው፤ ነጋ ጠባ የማይፈጸም ቃል መግባቱን ቀጥሎበታል። “ለምን አልፈጸምክም?” ብሎ መንግስትን አፋጥጦ ለመጠየቅ ህዝብ ወኔ አጥቷል። አሊያም በተደጋጋሚ በደረሰበት ውስብስብ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ምስቅልቅል፣ ቁምስቅሉን እያየ፤ ያረገው ነገር ቸግሮታል። አንገቱን ደፍቷል!

ያውቃሉ የተባሉት ምሁራንም ዱሮ ይባል እንደነበረው፡- “እናውቃለን። ብንናገር እናልቃለን!” የሚሉ ይመስላል። ወይም ፍርሐት ቤቱን ሰርቶባቸዋል። ረዥም ዕድሜን ከዘለዓለማዊነት እያምታቱ (They took longevity for eternity እንዲሉ)፣ ያልፍልናል እያሉ ራሳቸው ያልፋሉ! የእርግማን እስኪመስልባቸው ድረስ አድር-ባይነትን፣ ስግብግብነትን፣ ሁሉን ለእኔነትን ተያይዘውታል! የሩቅ ምስራቅ ጠበብት፤ ”የአንድ ህብረተሰብ ጥንካሬ በምሁሩ መዓዛ ሽታ ይለካል” የሚሉት ብሂል፣ ለሀገራችን ምሁራንም መጠቀስ ያለበት ሀቅ ነው ብንል ከማጋነን አይጣፍብንም። በሌላ ጎኑ ደግሞ ከተፈጥሮም ጋር ትግል ይጠበቅብናል። ጎርፍ፤ ድርቅና የአየር መዛባት በተደጋጋሚ አባዜው አልለቀን ስላለ ለከባድ ቸነፈር እና ርሀብ መጋለጣችን በየአስርት ዓመቱ የምናየው ክፉ እጣ መስሎብናል። ይህን የሚቋቋም ብርቱ ጫንቃ ያለው ትውልድ ከመፍጠር ይልቅ፤ “ንጹሃን ዜጎች በግፍ ተጨፈጨፉ” የሚል ዜና አዳምጦ ዝም የሚል ማህበረሰብ አቅፈንና አዝለን፤ መቀመጥን ሥራዬ ብለን ረዥም መንገድ ዳክረናል!

አሁን፤ያለፈው ይበቃን ዘንድ ወደፊት ለመራመድ መቁረጥ አለብን። የመለወጥ ድፍረቱ ሊኖረን ይገባል። ድህነትንም ሆነ ድህነትን የሚያመጣብንን ሁሉ ለመቋቋም መነሳት ግድ ነው። በአንድ በሀገር ጉዳይ ሁላችንም ተጠያቂ መሆናችንን አንርሳ። ያየነውን አይተናል ለማለትና እንከንም ካለበት ለመጠቆም፤ ለመዋጋት ወደ ኋላ አንበል። እንድፈር፤ እንነጋገር።

“አሁን ለምንድነው፤ ፈሪ ማቅንቀኑ
ቅጠል አይበጠስ፤ ካልደረሰ ቀኑ!”

ያሉ አባቶች ያቆዩዋት አገር እንደሆነች አንርሣ! መንገድ ካልጀመሩት አይገፋም፤ ወንበር ካልያዙት የማንም መቀመጫ ነው! አልት በዉሃ ይወድቃል እንዲሉ፣ ለሁሉም በዚህ ዘመን፤ ልብና ልቦና ይስጠን!

ከአዲስ አድማስ መስከረም 28 ቀን 2015 ዓ.ም እትም የተወሰደ

# በፍጥነት ሥራ ለማግኘት ትፈልጋለህ?

ሁልጊዜ ጥሩ ሥራ ሊያገኝ የሚችል ሰው የተሻለ ብቃትና ልምድ ያለው ሰው ብቻ አይደለም። ብዙውን ጊዜ ሥራ የሚያገኘው፣ ሥራ በመፈለግ ረገድ የተዋጣለት ሰው እንደሆነ ሞያተኞች ይናገራሉ። አንተስ ስራ ተፈልጋለህ? እንግዲያዉስ ሥራ በመፈለግ ረገድ የተዋጣልህ እንድትሆን፣ ከዚህ በታች የተመለከቱ ምክሮችን ተከተል።

1) በመጀመሪያ በአካልና አዕምሮ ዝግጁ ሁን

ከጥሩ ሥራህ ተፈናቅለህ ከሆነ ወይም ደግሞ ለተወሰኑ ጊዜያት ያለ ሥራ ተቀምጠህ ከነበረ በቀላሉ ተስፋ ልትቆርጥ ትችላለህ። ብዙ ሰዎች ከሥራ ሲባረሩ ወይንም ሲለቁ ሌላ ሥራ እንደሚያገኙ ሙሉ እምነት ይኖራቸው ይሆናል። ሆኖም ግን ወራት እያለፉ ሲሄዱ ሥራ ማግኘት ይቸገራሉና ጭንቀት ይይዛቸዋል፡፡ ከዚያ በኋላ ድብርት ይጫናቸውና፣ ይመራቸዉና ከጓደኞቻቸው ጋር እንኳን መነጋገር ይከብዳቸዋል። ታዲያ የተስፋ መቁረጥን ስሜት ለመከላከል ዕለቱን ምን ስትሠራ እንደምትውል ለማወቅ የራስህን ‘የሥራ’ ፕሮግራም ማውጣት በጣም አስፈላጊ ነው። የዕለት የዕለት ግቦችን አውጣና ያከናወንከውን ነገር በጽሑፍ አስፍር ከዚያ በኋለ በእያንዳንዱ ቀን የዕለቱን እንቅስቃሴህን ከመጀመርህ በፊት ልክ ሥራ ስትሄድ እንደምትለብሰው ዓይነት አለባበስ መልበስ አለብህ ይላሉ በዘርፉ ጥናት ያደረጉ ሰዎች። ምክንያቱም ተገቢ አለባበስ መልበስህ ስልክ በምታወራበት ጊዜም እንኳን በራስ የመተማመን ስሜትህ እንዲጨምር ያደርጋልና። ሥራ ሳታገኝ ምንም ያህል ጊዜ ቢያልፍ ሥራ መፈለጉን ሥራዬ ብለህ ልትይዘው ይገባል። በዚህ መልኩ በተደራጀ መንገድ ሥራ መፈለግ በራስ የመተማመን ስሜትህን ስለሚጨምር የሚስማማህን ሥራ ለመፈለግ ጥሩ ስሜት ይኖርሃል፣ ተግብረዉ።

2) ክፍት የሥራ ቦታዎች አጠያይቅ

በጣም ትልቅ መረብ ያለው ዓሣ አጥማጅ ዓሣ የመያዝ አጋጣሚው ሰፊ ነው።አንተም በተመሳሳይ "መረብህን" እንዴት ማስፋት እንደምትችል ማወቅህ ሥራ የማግኘት አጋጣሚህን ከፍ ያደርገዋል። ሥራ ለማግኘት የምትጥረው በጋዜጣ ወይም በኢንተርኔት የሚወጡ ማስታወቂያዎችን በመከታተል ብቻ ከሆነ መረብህ ትንሽ ስለሚሆን በርካታ የሥራ አጋጣሚዎች ያመልጡሃል። ስለዚህ ክፍት የሥራ ቦታዎች ማወቅ የሚቻለው ማስታወቂያዎችን ተከታትለህ ከማመልከት በተጨማሪ ለአንተ የሚሆን ሥራ ይኖራቸው ይሆናል የምትላቸውን ድርጅቶች በስልክም ሆነ በአካል ለማነጋገር በየሳምንቱ ጊዜ መመደብ አለብህ። ማስታወቂያ እስኪያወጡ ድረስ አትጠብቅ። የድርጅቱ አስተዳዳሪዎችን ሐላፊዎች ሥራ እንደሌለ ቢነግሩህም ሌላ የሚያውቁት ቦታ ካለ እንዲጠቁምህ፤ ማንን ማናገር እንዳለብህ እንዲነግሩህ ጠይቃቸው። ጓደኞችህ፣ ዘመዶችህና የምታውቃቸው ሌሎች ሰዎች ማስታወቂያ ላይ ያልወጡ ክፍት የሥራ ቦታዎችን ያውቁ እንደሆነ መጠየቅም ሌላው አማራጭ ነው።

3) የተለያዩ ለውጦችን አስብ

ሥራ የማግኘት አጋጣሚህ ከፍ እንዲል እንደ ሁኔታው ለውጥ ማድረግ መቻል አለብህ። እንደ ሁኔታው ለውጥ ማድረግ ሲባል ምናልባት ለአንዳንድ ሥራዎች ያለህን ጥላቻና ንቀት ማስወገድ ማለት ሊሆን ይችላል። በሶስዮሎጂ የተመረቅህ እንደሆነ ከዚህ ዘርፍ ውጭ ያሉ የተለያዩ ሥራዎችን ለማፈላለግ ራስህን አዘጋጅ፡፡ እስከጊዜው ድረስ እንኳን ማንኛውንም ተስማሚ ሥራ መቀበልን ልትማር ይገባሃል፡፡ በሂደት በሰለጠንህበት ሙያ ሥራ ልታገኝ ትችላለህና፡፡ ከሥራ የተገለልክ እንኳ ብትሆን የቀድሞውን ዓይነት ሥራ ማግኘት አለብኝ ብለህ አትድረቅ፡፡ ማንኛውንም ሥራ፣ ሌሎች ዝቅተኛ አድርገው የሚመለከቱትንም ጭምር ለማግኘት የሚያስችሉህን አጋጣሚዎች ሁሉ በመከታተል ተጠቀምባቸዉ፣ ይጠቅምሃል።

4) ውጤታማ ሲቪ አዘጋጅ

ብዙዉን ጊዜ ሥራ ለመቀጠር የሚያመለክቱ ሰዎች የተማሩትን ትምህርትና የሥራ ልምዳቸውንና ሌሎች ጉዳዮችን የሚገልጽ ሲቪ አዘጋጅቶ ማሰራጨት ያስፈልጋቸዋል። የሆነ ሆኖ የምትፈልገው ሥራ ምንም ዓይነት ቢሆን በጥሩ ሁኔታ የተዘጋጀ ሲቪ ላቅ ያለ ጠቀሜታ አለው። በመሰረቱ ሲቪ ቀጣሪዎችህ ስለማንነትህ እንዲያውቁ ብቻ ሳይሆን ቀደም ሲል ምን እንዳከናወንክና ለምን ዓይነት ሥራ እንደምታስፈልጋቸው ሊያሳውቃቸው ይችላል፡፡ ሲቪ በተለያየ መልክ ሊዘጋጅ ይችላል፡፡ የተለመደው የሲቪ አዘገጃጀት ሙሉ ስምህን፣ አድራሻህን፣ ስልክ ቁጥርህን፣ የኢ-ሜይል አድራሻህንና የተወለድክበትን ቀን፤ ምን መስራት እንደምትፈልግ፤ የተማርከውን ትምህርት፤ እንዲሁም ከምትፈልገው ሥራ ጋር በተያያዘ ያገኘኸው ሥልጠናና ያዳበርከው ችሎታ ሊያካትት ይችለል። ቀደም ሲል ያገኘኸውን የሥራ ልምድ በዝርዝር ዘግብ። ያደረግኸውን ብቻ ሳይሆን የደረስክባቸውን አንዳንድ ግቦችና ለቀድሞ ቀጣሪዎችህ ምን ጥቅም እንዳስገኘህላቸው አስፍር። በተጨማሪም አሁን ለምትፈልገው ሥራ ብቁ ያደረጉህን የቀድሞ ሥራህ ገጽታዎች ጎላ አድርገህ ጥቀስ። ባሕሪህን፣ ፍላጎቶችህንና በትርፍ ጊዜ ማድረግ የምትወደውን ነገር የሚመለከቱ የግል ጉዳዮችን ጨምረህ ጻፍ። በነገራችን ላይ ሁሉም ድርጅቶች አንድ ዓይነት ነገር ስለማይፈልጉ ከእያንዳንዱ የሥራ ማመልከቻህ ጋር የምታያይዘውን ሲቪ የተለያየ ማድረግ ብልህነት ነው። ሲቪ የሚዘጋጀው ልምድ ላለው ሰራተኛ ብቻ አይደለም፡፡ አዲስ ሥራ ፈላጊ ከሆንክ ሲቪ ማዘጋጀት ይኖርብሃል። እንደ ሥራ ልምድ ሊቆጠሩ የሚችሉ በትርፍ ጊዜህ ያከናወንካቸው የተለያዩ ጉዳዮችህንና የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሊኖሩህ ይችላልና ሲቪ ማዘጋጀት ተገቢ ነው። ሲቪ ማዘጋጀት አመቺ ባልሆነበት አጋጣሚ እንኳን ቢዝነስ ካርድ የመሰለ ስምህን፣ አድራሻህን፣ ስልክ ቁጥርህን፣ የኢ-ሜይል አድራሻህን በአጭሩ የሚገልጽ ካርድ ሊቀጥሩህ ለሚችሉ ሰዎች ትተህ መሄድ ሌላኛው መደረግ ያለብት አማራጭ ነው።

5) ራስን በሚገባ ለቃለ መጠይቅ አዘጋጅ

ለቃለ መጠይቅ ከመዘጋጀትህ በፊት ያመለከትህበትን ድርጅት በሚገባ ማወቅና መመራመር አለብህ። ስለ ድርጅቱ ይበልጥ ስታውቅ በቃለ መጠይቁ ወቅት ስኬታማ የመሆንህ አጋጣሚ ያንኑ ያህል ከፍ ይላል። በተጨማሪም ስለ ድርጅቱ በጥልቀት ማወቅህ ድርጅቱ በእርግጥ አንተ የምትፈልገው ዓይነት ሥራ እንዳለው ወይም እዚያ መሥሪያ ቤት መሥራት እንደሚገባህም ለማወቅ ያስችልሃል። ቀጥሎ ደግሞ በቃለ መጠይቁ ወቅት ምን እንደምትለብስ አስብ። የምትፈልገው ሥራ የባንክ ከሆነ ከዚህ ጋር የሚስማማ ሥርዓታማና ንጹሕ አለባበስ ይኑርህ። የግድ ውድ ሊሆን ግን አይገባም። ሥርዓታማ አለባበስና አጋጌጥ ያለህ መሆኑ ቀጣሪው ለራስህ አክብሮት እንዳለህና በዚህም የተነሳ ሥራህን በአክብሮት ልትይዝ እንደምትችል እንዲገነዘብ

ያደርገዋል። ቃለ መጠይቅ ከምታደርግበት ሰዓት 15 ደቂቃ ቀድመህ በቦታው መገኘት ጥሩ ነው፡፡ በእርግጥ በጣም ቀደም ብሎ መገኘቱ ጥሩ አይደለም። ይሁን እንጂ ዘግይቶ ከመድረስ ግን ይሻላል፡፡ ቃለ መጠይቅ የሚደረግባቸው የመጀመሪያዎቹ ሦስት ሴኮንዶች ወሳኝ እንደሆኑ ባለሙያዎቹ ይናገራሉ። ቃለ መጠይቅ የሚያደርግልህ ሰው በዚያች አጭር ጊዜ ውስጥ፣ ለአንተ በሚኖረው አመለካከት ላይ ከባድ ተጽዕኖ የሚያደርጉትን አቋምህንና ጸባይህን ይገመግማል። ዘግይተህ መድረስህ በከፍተኛ ሁኔታ አሉታዊ ግምት እንዲሰጥህ ምክንያት ይሆናል። መጀመሪያ የተፈጠረውን አመለካከት ማስተካከል የሚቻልበት ሁለተኛ አጋጣሚ እንደሌለ አስታውስ። ሌላው ማስታወስ ያለብህ ነገር ቃለ መጠይቅ የሚያደርግልህ ሰውን የሰማይ ያህል አክብደህ አትየው። እርሱም ቢሆን ሥራውን ያገኘው በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ አልፎ ሊሆን ስለሚችል ምን እንደሚሰማህ ያውቃልና ፍርሐት ሊሰማህ አይገባም። እንዲያውም ቃለ መጠይቅ እንዴት ማድረግ እንደሚችል ያገኘው ሥልጠና ጥቂት ሊሆን ወይም ደግሞ ጨርሶ ሥልጥኖ ላያውቅ ስለሚችል ይደናገጥ ይሆናል። ቃለ መጠይቅ የሚያደርግልህን ሰው ፈገግ በልና ጠበቅ አድርገህ በመጨበጥ ሰላምታ ስጠው። በቃለ መጠይቁ ወቅት ቀጣሪው ምን እንደሚጠብቅብህና ምን ዓይነት ችሎታ እንዲኖርህ እንደሚፈልግ በትኩረት ተከታተል እንጂ አትቁነጥነጥ ወይም አካሄድህ፣ አቋቋምህና አቀማመጥህ ከሥርዓት ውጪ አይሁን፤ ጥሩ አቋም መያዝህ በራስ የመተማመን መንፈስ እንዳለህ የሚያሳይ ስለሆነ በጣም ዘና ሳትል ወይም ከልክ በላይ ሳታወራ፤ እንዲሁም ጸያፍ አነጋገር ሳትጠቀም ቃለመጠይቅህን ፈጽም። በተጨማሪም ስለ ቀድሞ አሠሪህና የሥራ ባልደረቦችህ አሉታዊ ነገር አትናገር፤ ስለ እነርሱ አሉታዊ ነገር ካወራህ ቃለ መጠይቅ የሚያደርግልህ ሰው ይህንንም ሥራ በተመለከተ አፍራሽ አመለካከት እንደሚኖርህ ሊሰማው ስለሚችል ልብ ልትል ይገባል። ቃለ መጠይቅ የሚያደርግልህን ሰው ዓይን ዓይኑን መመልከት፤ በምትናገርበት ጊዜ የራስህ የሆነ አካላዊ መግለጫ መጠቀም፤ በግልጽ መናገር ጥሩ እንደሆነ ባለሙያዎቹ ይናገራሉ፡፡ ቃለ መጠይቁ ካበቃ በኋላ ሥራውን ከልብህ የምትፈልገው መሆኑን መናገር ጥሩ ማርክ ሊያሲዝልህም ይችላል።

ከላይ የተዘረዘሩትን ሐሳቦች ተግባራዊ ካደረግክ በቅርቡ ሥራ ታገኛለህ፣ ያዉም ጥሩ ስራ፣ ባለቤት የሚያደርግ። ሲሳካልህ፣ ሌሎችን አትርሳ።

ካነበብነው




# የዕፅዋት የሚስጥር ቋንቋ

ዐለም ከተጠፈረ ጀምሮ በተለያዩ ጊዜያት ዕፅዋት የማይጨበጥና ሓሳባዊ (Mystical & Romantic) ባህርይ ሲሰጣቸው ቆይቷል፤ ዕፅዋት በግልጽ የሚታይ ምልክትም አላቸው። ለምሳሌ ነጭ አበባ ንፅህናን ያመለክታል፣ አልፎ አልፎ፣ ከጊዜ ብዛት የመጀመሪያው ትርጉማቸው እየተረሳ ሄዷል ለምሳሌ ሐምራዊ ማስተዋልን ያመለክታል። በመካከለኛው ክፍለ ዘመናት ሥዕልም ወይም ስእል መሳል የሆነ ትርጉም ነበረው። ይህም በመሆኑ ምንም እንኳ በወቅቱ ብዙኀኑ መሃይም ቢሆኑም ያነቡ ነበር ማለት ይቻላል። ምክንያቱም በማየት ብቻ እያንዳንዱ ዕፅ ምን ትርጉም እንዳለው ያውቁ ነበርን! በቪክቶሪያ ዘመን መንግሥት (Victorian era) አበቦችን በሰዎች መካከል ለመገናኛነት በመጠቀም ከፍተኛ ደረጃ የተደረሰበት ወቅት ነበር። ለምሳሌ በጥንቃቄ የተዘጋጀ የአበቦች እስር ወይም አንዱ ዘለላ አበባ፣ በፍቅረኞች መካከል መለዋወጥ፣ ያለምንም ጽሑፍ ተፈላጊውን መልዕክት ያደርስ ነበር። ከሁሉም አበቦች ይልቅ ጽጌረዳ በጣም የታወቀና ምስጢር ገላጭ ነበር፤ አንድ ወዳጅ ነጭ ጽጌረዳ ለፍቅረኛው የላከ እንደሆነ “I’m worthy of you” የሚል ትርጉም ይሰጥ ነበር ግን ቢጫ ጽጌረዳ የላከ እንደሆነ ቅናት እንዳደረበት ያመለክታል። የተለያዩ አበቦች ቅንብር የብዙ መጻሕፍት ጥራዝ የሚሞላ ትርጉም ይይዛሉ፤ ነጭና ቀይ ጽጌረዳ በአንድ ላይ

ሲታሠር አንድ መሆንና ለጋብቻ ጥያቄ (proposal) እንደማቅረብ ይቆጠራል፤ የዕፅ አንበሳ ዝርያ፣ የፈካና ያልፈነዳ እምብጥ ቀይ ጽጌረዳ በአንድ ላይ ታስሮ ሲላክ ታማኝነትን ሲያመለክት ጉዳዩ በሚስጥር መያዝ እንዳለበት ያመለክታል። የስኮትላንድ አፈታሪክ ደግሞ ኮሻሽላ ምስጢራዊ ጦርነትን እንዳቆመ ይናገራል። ይህ አፈታሪክ እንደሚያስረዳው የዴንማርክ ወታደሮች ስኮትላንድን በሌሊት ለመውረር ዝግጅት ሲያደርጉ አንድ የዴንማርክ ወታደር ኮሸሸላውን ሲረግጥ፣ እሾካማ ሰለሆነ ድምፅ በማሰማቱ የስኮትላንድ ወታደሮች ነቅተው ወረራውን አክሽፉት። ይህም በመሆኑ ዛሬ ኮሸሽላ የስኮትላንድ ብሔራዊ አበባ ለመሆን በቅቷል።

የተለያዩ ዕጾች ትርጉም ካላቸው አበቦች ፍሬዎች ቅጠሎች ወዘተ ጋር የተዛመደ ነው። ለምሳሌ የሾላ ፍሬ ብዙ ዘር ስላለው የወላድነት ምልክት ነው፣ ዛሬ በዓለማችን ላይ ለብዙ ሕዝቦች በምግብነት የሚያገለግሉት ሩዝ፣ ስንዴ ገብስ የምድራችንን የተፈጥሮ ፀጋን ያመለክታሉ። ቅመማቅመሞች ደግሞ የተደበቀ ምስጢራዊ ትርጉም አላቸው። ለምሳሌ በሶብላ ጥላቻን፣ ሻይ ጥራትን፣ ቅሩንፉድ ክብርን፣ ድምብላል የተደበቀ ሀብትን፣ ከሙን ስስትን ወይም ደስታን፣ ስናፍጭ ግድየለሽነትን፣ ብርቱካን ሰጪነትን፣ ጦስኝ ድፍረትን ያመለክታሉ።

ለኢትዮጵያ ሆርቲካልቸራል ማህበር አ.አ.አ.የህዳር ወር 1990 የዜና ወረቀት ቁጥር 252 የተገኘና ከእንግሊዝኛ የተተረጎመ።

# How Ethiopia Tracks Date and Time

Ethiopia uses its own calendar which divides the year into 12 months of 30 days each, with the remaining five (or six days in a leap year) constituting a short 13th month of Pagme. The Ethiopian New Year commences on the 11th or 12th of September in the Gregorian calendar. There is a 7 or 8 year difference from the Gregorian calendar, seven years from September to January 1, and eight years from January 1 until September 11/12.

Locally, many Ethiopians use a different method of keeping time with Sunrise being 12 in the morning and sunset at 12 in the evening. Times are expressed as being "3 in the morning" (approximately 9 am at GMT+3) or "12 in the evening" (approximately 6 pm GMT+3). If you are visiting Ethiopia for a meeting or an event it can be important (at atime advisable) to confirm times to avoid confusion.

## Few Interesting Facts about Calgary:

1. Calgary's Stampede, also knows as the "greatest outdoor shown on Earth," is the largest rodeo events in the world
2. Calgary is at significant centre for Canada's oil and gas industry
3. Calgary Tower was once the tallest free-standing structure in the world
4. Calgary hosted the 1988 winter Olympics, making it a popular destination for winter sports enthusiasts.



Calgary 1988 Olympics | olympics.ca







# Interview with Sileshi Mekonen, 2022 Election Committee Chairman

አቶ ስለሺ መኮንን ይባላል፤ በካልጋሪ የኢትዮጲያ ማህበረሰባ ማህበር ውስጥና በከተማችን የስፖርት እንቅስቃሴ ውስጥ በተለያዩ ሃላፊነቶች ትልቅ አገልግሎትን ያበረከተ ኢትዮጲያዊ ነው፤ ባለፉት ሶስት የማህበሩ ምርጫዎች ላይ የአስመራጭ ኮሚቴ ሊቀመንበር ሆኖ አገልግሏል፤ እነኚህን የምርጫ ሂደቶች በተመለከተ ያጋጠመውን ልምድና ባጠቃላይ ስለማህበረሰባችን ሁኔታ የሚያስበውን ነገር እንዲያካፍለን መጽሄታችን ቃለመጠይቅ አድርጋለት ነበር፤ ቃለመጠይቁ እንደሚከተለዉ ይቀባል።

**ጥያቄ- ባለፉት የማህበሩ ምርጫዎች ላይ በአስመራጭ ኮሚቴ በሊቀመንበርነት ሰርተህ ነበር፤ ያጋጠመህ ተግዳሮት ምን ይመስላል?**

መልስ- እኔን የገጠመኝ ተግዳሮት በአብዛኛው የማህበሩ አባል ከመሆኔም ሆነ ከሆንኩ በኋላ ምርጫ በመጣ ቁጥር ጸብ አለ፤ ከፍተኛ የሆነ ረብሻ ይፈጠራል፣ ነገሮች ወደ ማይሆን እቅጣጫ ያመራሉ፣ ወደማይገባ ነገር ይደረሳል፤ የማህበረሰብ ጉዳይ መሆኑ ይቀርና የግለሰብ ጉዳይ ይሆናል፤ ነገር ግን ባለፈው ሶስት በተሳተፍኩባቸው ምርጫዎች በጣም በጣም ትልቅ ለውጥ ነው ያለው፤ ትልቅ መሻሻል አለ፤ ከዚያ በፊት እንዳውም እኔ የተሳተፍኩበት አንድ ምርጫ ላይ ሴኪዩሪቲ ሁሉ ቆሞ ነበር፤ ከዚያ በፊት የነበረው ችግር ደግሞ ይፈጠራል ከሚል ፍራቻ ነው ይህ የተደረገው፤ ያ ግን አልሆነም፤ የተሳተፈው ሰው

ስነስራት ነበረው፤ ምንም ረብሻ እልተፈጠረም፤ አመራረጣቸውም ልዩ ነበር፤ እሁን በቅርቡ በተደረጉት ሁለት ምርጫዎች ደግሞ ውስጥ ሴኪዩሪቲ ጭራሹን እልነበረም፤ ምንም አይነት ችግርም አልተፈጠረም፤ ይህ ያለውን መሻሻል ነው የሚያሳየው፤ አሁን እዚህ ላይ ተደርሷል፤ አሁንም ግን መሻሻል ያለባቸው ነገሮች አሉ፤ ስለዚህ ተግዳሮቱ ምን ነበር ላልሽኝ ምርጫ በሚካሄድበት ጊዜ በጋራ ግሩፕ ግሩፕ ሆኖ ካምፔይን ማድረግ የምርጫ ባህሪ ቢሆንም አንዳንድ አላስፈላጊ የሆነ የሰው ስም ማጥፋትና ስብእና ማቆሸሽ ነገሮችን ታዝቤአለሁ፤ ይህ መሆን የለበትም፤ እንዳልኩት የምረጡኝ ቅስቀሳው አይጠላም፤ እንዳውም እንደኔ ቢሆን ማበረታታት ነው የምፈልገው፤ ምክንያቱም ሰዎች የሚፈልጉትን ሰው፣ ይሰራል ብለው ያሰቡትን ሰው፣ ይመረጥ ዘንድ ካምፔን ማድረጋቸው ጥሩ ነው፤

**ጥያቄ - ካምፔይን ወይንም የምረጡኝ ዘመቻ ስትል ግን ከዘር፣ ከሀይማኖት ጋርየተያያዘ ነው ወይስ አይደለም?**

መልስ - የለም የለም፣ እኔ ከዛ አንጻር አላየውም፤ እርግጥ እንደዛ ሊመስል ይችላል፤ ለምን መሰለሽ አንዳንድ ጊዜ ካአገር ቤት አብሮን ተያይዞ የሚመጣ ወገንተኛ አስተሳሰብ በሁላችንም ውስጥ አለ፤ ያ ሃሳብና ስሜት ምናልባት አገራችን ውስጥ ከሚካሄደው ፖለቲካ ጋር የተያያዘ ነው ብለው ሰዎች እንደዛ ገምተው መጥተው ሊሆን ይችላል፤ በDecember 2022 በተኪያሄደዉ ማርጫ እኔ የምርጫው ሊቀመንበር ነበርኩኝ፤ በርግጥ አንዳንድ ምልክቶች ነበሩ፤ አልነበሩም ብዬ መካድ አልችልም፤ ግን ተጽእኖ ኖሯቸው ተፈጽሟል የሚል እምነት የለኝም፤ አልተፈጸሙም፤ ምልክቶች ነበሩ፣ አቅጣጫ ይዘው ግን በተግባር አልተፈጸሙም፤ ምርጫ ላይ ያ ነገር አልነበረም፤ ያ ማለቴ ይህ ነገር በምርጫው ውጤት ላይ አልተንጸባረቀም ማለቴ ነው፤ ምልክቶቹ በምርጫው አካሄድ ላይ ይታዩ ነበሩ ወይ ለሚለው አዎን ነበሩ፤ ቅድም እንዳልኩት እኔ በግሌ ግሩፒንግ ወይንም መቧደን ማለት ምርጫ ሲደረግ የተለመደ ነገር ነው፤ እዚህም እገር ኮንሰርቫቲቭ፣ ሊበራል፣ ኤንዲፒ ተብሎ የምረጡኝ ዘመቻ እንደሚደረገው ማለት ነው፤ ይሰራልኛል ብዬ ያሰብኩትን ሰው እኔም በግሌ ሰዎችን ፈልጌ ቀስቅሼ እንዲመረጥልኝ እሞክራለሁ፤ በጣም ፖዘቲቭ የሆነ ነገር ነው፤ ግብአቱም ጥሩ ይሆናል፤ ይህ መሆኑ ግድ ነው፤ ጥሩ ነው፤ አሁን ለእጩነተ እየቀረቡ መጥተው ምናልባት ባልመረጥስ በሚል አንዳንዶቹ መፍራት ጀመሩ፤ ተግዳሮት ያልኩሽ ይህንን ነው፤ ከዛ በኋላ ላልመረጥ እችላለሁ የሚል ስሜት ውስጥ ገቡና ያንን የተሸናፊነት ስነልቦናና ስሜት ማንጸባረቅ ጀመሩ፤ እንግዲህ እንደሰው ምን ይሆናል መሰለሽ ወደሌላ አቅጣጫ አመሩ፤ ያ አቅጣጫ ምንድነው ብለሽ ብትጠይቂኝ መጨረሻ ሰአት ላይ የምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴው ላይ ጥያቄ ማንሳት ጀመሩ፤ ምርጫውን ራሱን ጥያቄ ውስጥ ከተቱት፤ እንዴት ይካሄዳል? ሕጋዊ ነው ወይ? እነኚህ የምረጡን ዘመቻ ሲያካሂዱ የነበሩ ሰዎች ናቸው እኮ! አሁን አየሽ እዚህ ላይ ነው ስህተቱ፤



**ስለሽ መኮነን**

**ጥያቄ- ውጤቱ ላይ ነው ጥያቄ የነበረው?**

መልስ - ጥያቄአቸው የነበረውማ ወደ ውጤቱ በሚወስደው ሂደት፣ በፕሮሰሱ ላይ ነበር ፤ ጫፍ ላይ ስንደርስ፤ በጊዜው በተለያዩ ምክኛቶች በአካል መገናኘትና መሰብሰብ የማይቻል ስለነበረ እኛ እጩዎችን በዋትሳፕ መድረክ ላይ እየተቀበልን ነበር፣ በዚህ መድረክ ላይ እጩ እያቀረቡ የነበሩ ( ሁለት ሶስት ነበር ግሩፑ) አንደኛው ተፎካካሪ ተብሎ የሚገመተው ግሩፕ የነበረው አሁን ካለው ፕሬዚዳንት ጋር ተፎካክሮ ውጤት ላይ ይበቃል ብለው ያሰቡት ግሩፖች የጠበቁት ውጤት እንደማይመጣ ሲገባቸው ወደ ሌላ አቅጣጫ አመሩ፤ የስም ማጥፋትና ምርጫውን የማሰናከል አካሄድ ጀመሩ፤ ይሄም አቅጣጫ የበታችነት ስሜት (ኢንፌሪዮሪቲ) የፈጠረባቸው ነው፤ ይህ በፍጹም መሆን አልነበረበትም፤ በዛው ቢቀጥሉ ማን

ያውቃል? ሊያሸንፉ ይችሉ ነበር .... ግን ወዲያውኑ ከሰላማዊ የምርጫ አቅጣጫ ወጡና ሰዎችን በተለይ እኛን...እገሌ እንደዚህ፣ እገሌ እንደዚህ ብለው ወደማያስፈልግ የስብእና ማጠልሸት ነገር ላይ ተጠመዱ፤ . ወደፊት ይሄ ነገር እንዲህ ባይሆን ጥሩ ነው.፤ በነገርሽ ላይ በሂደት ውስጥ አምነው የነበሩ ሰዎች፣ ማህበሩ ውስጥም አባል የነበሩ ሰዎችም፣ እነኚህ ቡድንተኞች እርስበርስ ተመራርጠው የመጡ ሰዎች መሆናቸውን አስቀድመው ጥቆማ ሰጥተውናል፤ ...እገሌ ብለው ስም መጥራት ነበር ያቃታቸው እንጂ ብዙ ነገር ተብሏል፤ ፤ "ያልተስማማችን አለች " ይላሉ፤ ይህ ማለት ምን ማለት ነው? ስለ ሴት አይደለም የሚያወሩት? በምርጫው ላይ በእጩነት ከቀረቡት ውስጥ አንድ ሴት ብቻ ነበረች፤ ስለዚህ የሚያወሩት ስለሷ ነው ማለት ነው፤ አሁን እሷን ወደ ማጋለጥ ተመጣ፤ ሊሆንም ላይሆንም ይችላል፤ እኔ እስካሁን ነገሩ እንደዚህ ነው ብዬ ለማመን ይቸግረኛል፤ ዋናው ነገር ከዚህ ልምድ የተማርኩት ውጤቱ ምንም ይሁን ምን አንድ ጊዜ የምርጫ ሂደት ተጀምሮ ድምጽ ከተሰጠና ተቆጥሮ ውጤቱ ይፋ ከሆነ በኋል ውጤቱን አክብሮ ወደ ስራ መግባት ብቻ ነው፤ ከፈለጉ በሚቀጥለው ምርጫ በደንብ ተዘጋጅተው መጥተው መወዳደር ይችላሉ፤ በባህሪያችን እንደማህበረሰብ ይህ ልምድ የለንም፤ መዳበር ግን አለበት ብዬ አምናለሁ፤

**ጥያቄ- ምርጫው ሴትን ያካተተ ነበር?**

መልስ - እዎን፤ በርግጥ አካትቷል፤ ለምርጫ ከምትጠቁሟቸው ሰዎች ውስጥ ሴቶችን እንዲጨምሩ እናበረታታ ነበር፤ ይህንን ስልሽ ሴቶቹ ዝም ብሎ ለቁጥር ማሟያ ብቻ እንዲሆኑ አስበን አልነበረም

**ጥያቄ - የተመራጭነት ማሟያ መስፈርቱ ምን ምንን ያጠቃለለ ነበር?**

መልስ- ትልቁና ዋናው መስፈርት ከሶስት ወር በላይ አባል መሆን ያስፈልጋል፤ ሌላው መስፈርት ተጨማሪ ግብአት ነው፤ ለምሳሌ በአስተዳደር ላይ ልምድ ያለው/ያላት፣ በዩኒቨርሲቲ ወይም በኮሌጅ ደረጃ የተማረ/የተማረች፣ ለማህበረሰቡ አገልግሎት ያደረገ/ያደረገች ቢሆኑ ጥሩ ነው፤ እነኚህ ግን ወሳኝ መስፈርቶች አልነበሩም፤ ዋናው መስፈርት የነበረው አባል ሆኖ ሶስት ወር የሞላው የሚለው ነበር፤ እንግዲህ ቅድም ያልኩት የምርጫው ተግዳሮት ሰዎች በምርጫው ያለማሸነፍ ነገር ሲሰማቸውና በዚህም የበታችነት ስሜት ሲያጠቃቸው ምርጫውን ለማጣጣል ሞክረዋል.

**ጥያቄ - በጣም እመሰግናለሁ፣ ህብተረሰቡ ወደ ማህበሩ እንዲመጣ ምን መደረግ አለበት ትላለህ? ከማህበሩስ ምን ይጠበቃል?**

መልስ - ኮሚኒቲ ስንል እንግዲህ ሁሉ ያቀፈ ማህበረሰብ ነው፤ ማህበረሰብ ማለት ደግሞ አንድ ሰው ወይም ሁለት ሰው ማለት አይደለም፤ ማህበረሰቡ ኮሚቴ ማለትም አይደለም፤ እያንዳንዱ አባል፣ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ እዚህ ከተማ የሚኖር ሁሉ ማህበሩን የመቀላቀል መብትም ግዴታም አለበት፤ በጋራ ሲኮን፣ ብዙ ቁጥር ሲታይ በህብረት የተደረገ ነገር ሁሉ ሁልጊዜ ጥንካሬ አለው፤ መቆምም የሚቻለው በጋራ ነው፤ አንድ እግር ብቻውን አይቆምም፤ አንድ እንጨትም ያናድ እንጂ አይነድም ነው የሚባለው፤ ስለዚህ ለጠየቅሽኝ ጥያቄ እንደ ኮሚቴ በርግጥ ልጓም ያለባቸው ነገራ አለ፤ የቦርድ አባላት አንድ ነገር ወደታች በሚያወርዱበት ጊዜ የመቃወም፣ ነገሩን ፈጥኖ የመተቸት ነገር አለ፤ ያም ቢሆን ግን ያንን ተቋቁሞ ማለፍ አለባቸው፤ በርግጥ በአገራችን ውስጥ የሚታየውና የሚደረገው ነገር እዚህ ከተማና ህይወታችን ላይ ይንጸባረቃሉ፤ ፖለቲካው ብትይ፣ የዘሩ ነገር ብትይ፣ ሃይማኖቱም ብትይ፣ (በርግጥ አሁን የሀይማኖቱ ፖለቲካ ትንሽ ጋብ ብሏል) ፤ የዘሩ ፖለቲካ ግን ሙሉ በሙሉ እዚህም አገር ቤትም ይንጸባረቃል፤ እኔ ግን የምለው ምንድነው ኢትዮጵያዊ እስከሆንን ድረስ ሁላችንም ኮሚኒቲያችን ውስጥ የመሳተፍ ግዴታ አለብን፤ ብዙ ጊዜ ችግር የሚፈጥሩት ብዙም የማይታወቁ ወይንም ኮሚኒቲውንም (ማህበርሰቡንም) ሆነ ማህበሩን አገልግለው የማያውቁ ሰዎች ናቸው፤ አሁን ግን እኔ በተሳተፍኩባቸው ሶስት ምርጫዎች በጣም ትልቅ ለውጥ አይቻለሁ፤ የሚገርምሽ ነገር በመጀመሪያ ላይ በተሳተፍኩበት ምርጫ ላይ ሴኪዩሪቲ ተቀጥሮ ረብሻ እንዳይፈጠር ይጠብቅ ነበር፤ በኋላ ግን በነበሩት ምርጫዎች ላይ ሁሉም ስነስርአት ይዞ ያለምንም ችግር ምርጫ ማካሄድ ተችሏል፤ ነገሮች በጣም ተሻሽለዋል ማለት ነው፤ ብዙ ጊዜ ሰዎች በተለይ ወጣቶች ኮሚኒቲውን ማገልገል እየፈለጉ ጭቅጭቅና ረብሻውን በመፍራት ብቻ ወደኋላ እንደሚሉ ሰምቻለሁ፤ አሁን ግን ከሞላ ጎደል ጥሩ ለውጦች እየታዩ ስለሆነ ኢትዮጲያዊያንና ትውልደ ኢትዮጲያዊያን የሆኑ ሁሉ መጥተው ማህበራቸውን ያገለግሉ ዘንድ እመክራለሁ።



Members of the 2022 Election Committee and Observers at Work



Election Committee Members and Observers with the President Elect



The Presentation of Certificate of Recognition to Ato Molalet Abera for his Community Support during the Celebration of Ethiopian New Year in 2019



Sheik Umer and Church Leaders - Ethiopian New Year, 2019



A Discussion with Police on Youth Addiction, 2017




Celebrating Black History Month, February 2018



Some Members of the Former Leadership During the Inaguration Cermony of the Community Center in September 2021



The Inaguartion Cermony in Sepetmber 2021

# Interview with Samuel Tadesse, Former President of the Assocation

**ጥያቄ - ኮሚኒቲአችን የተመሰረተበትን 40ኛ አመቱን በዚህ አመት ያከብራል። እነ አንድ በካልጋሪ የሚኖር ኢትዮጲያዊና እንደገና ደግሞ በኮሚኒቲው ውስጥ በትልቅ ሀላፊነት እንዳገለገለ ሰው ምን ይሰማሀል?**

በመጀመሪያ ሃሳቤን እነዳካፍል እድሉ ስለተሰጠኝ፣ ምስጋናዬን ማቅረብ እፈልጋለሁ። ምንም እንኳን የእድሜውን ያህል መድረስ ያለበት ቦታ ባይደርስም፣ እዚህ ለመድረስ ከፍተኛ መስዋእትነት ከፍለው እዚህ ደረጃ ያደረሱት የአሁን አመራሮች ብቃት ምስክር ነው። ለዚህም ከፍ ያለ እውቅና ይገባቸዋል። እና በግሌ ይህንን ማህበር በጣም እንደሚወድ ግለሰብ በጣም ደስተኛ ነኝ።

**ጥያቄ - የማህበሩ ሊቀመንበር ሆነህ ባገለገልክበት ዘመን ስኬታማ ሆነናል ወይንም አልሆንም የምትላቸው ነገሮች አሉ?**

ስኬታማ ማለት ምን ማለት ነው? ለኔ ስኬታማ የምለው፣ በተለይ ማህበራችንን በተመለከተ፣ እንደ ዱላ ቅብብል ሩጫ፣ መሮጡ ብቻ ሳይሆን፣ ለተቀባይ አስተካክሎ መስጠት መቻል ያካትታል። እኛ ባገለገልንበት ወቅት ከላይ የተጠቀሱትን ጨምሮ ሌሎችንም በቅንነት ሰርተናል። ግን ጠንካራ ፖሊሲዎችና guidelines በመቅረጽ ለተረከበን ግሩፕ ማስተላለፍ አልቻልንም። ለዚህም ምክንያት ስደረድር መዋል እችላለሁ። At the end of the day, ግን መሰራት ያለበት ስራ አልተሰራም። ለዛም ነው ከዛ በኋላ የተፈጠሩት ምስቅልቅልና መዳከም የተፈጠረው። ይህን ስታይ የሮም አወዳደቅን ያህል ነው የወደቅነው። short term በሰራናቸው ስኬታማ ሆነን ይሆናል፣ long term እና ቀጣይነቱን በማረጋገጥ ግን፣ በሚገባ አልተሰራበትም።

**ጥያቄ - አርአያ ኢትዮጲያዊያን የሚል ፕሮጀክት ጀምራችሁ የተወሰኑ ኢትዮጲያዊያንን ምስጋና ሽልማት ማበርከታችሁን ሰምቻለሁ። ቲያትርና ባህላዊ ዝግጅቶችንም እያዘጋጃችሁ በርካታ ህዝብ ወደ ማህበሩ እየመጣ እንዲዝናና እና እንዲቀራረብም አድርገህ ነበር የሚል አስተያየት ሰምቻለሁ። እስቲ ትዝታህንና ልምድህን ለአንባቢዎች ብትገልፅ?**

በጣም ጥሩ ጊዜ ነበር። ብዙ ስራ፣ እቅድና ድካም አለበት። ከሁሉ በላይ ግን የመንፈስ እርካታ የሚሰጠኝ አብረውን ደከመን ሳይሉ በቮለንቲር የተባበሩን ነው። ሁሉንም ሁሌ አስታውሳቸዋለሁ። እነዚህን ሳስብ የአገልግሎት ጊዜየን እንደምርቃት እወስደዋለሁ። ስለራሴ ጥንካሬ ፣ ደካማ ጎን፣ ትእግስት መጠን፣ የመማርና አዲስ ነገርን የመቀበል፣ የፈጠራ ችሎታ የተረዳሁት ጊዜ ነበር። ይህ ደሞ ከሁሉም በላይ ነው። ከማይረሱት ተሳታፊዎች የማልረሳቸው ብዙ ቢሆኑም ጥቂቶች ለመጥቀስ ያህል፣ ህሩይ ክፍሌ፣ የድሮ ኢትዮ ስታሮች፣ አብነውና ዓለምፀሃይ፣ ታደሰ፣ ሲሳይ፣ አቢሲኒያ እግርኳስ ቡድን፣ ጋሽ በየነ፣ ትያትር ላይ የተሳተፉት ሙሉጌታ፣ ተሻገር ፣ ፌቨን፣ አማርኛ በማስተማር ዚያድና ሙሉጌታ። ስንቱን ልጥቀስ። በዚህ አጋጣሚ፣ አብራችሁ ለሰራችሁ በሙሉ ከፍ ያለ ምስጋናዬን ማቅረብ እወዳለሁ። ከሁላችሁም ብዙ ነገር ተምሬአለሁ። እግዚአብሔር ያክብርልኝ።

**ጥያቄ - ማህበራችንን ወደፊት ለማሳደግ ምን መደረግ አለበት ትላለህ?**

ማህበር ከላይ እንደጠቀስኩት እንደዱላ ቅብብል ሩጫ ነው። ለሚቀጥለው ተቀባይ አመቻችቶ መስጠቱ ቀጣይነቱን ያረጋግጣል። ጠንካራ ማህበር በሚኖሩት policy and guidelines የየቀን ተግባራቱን መስራት አለበት። እነዚህ ከቀረቡለት የሚቀጥለው ተረካቢ አመራር ደካማ ቢሆን ያለውን ለማስቀጠል በቀላሉ ይችላል። ባለራዕይ አመራር ከሆነ ደግሞ፣ ባሉት ላይ ጨምሮ ማህበሩን ማጠናከር ይችላል። ከነዚህ guidelines ጋር accountability መኖር ይኖርበታል። ይህ ደግሞ ነገሮች ከመበላሸታቸዉ በፊት እግርበግር ለማስተካከል እድል ይፈጥራል። አባላትም ተመርጠው ማገልገል የራሳቸውን አእምሮ የሚያሳድግና የሕይወት ልምዳቸው ስለሚያሳድግ ወደኋላ እንዳይሉ አደራ እላለሁ።

**ጥያቄ - የመጨረሻ መልዕክት ካለህ?**

አሁን ያለው አመራር ጠንክሮ ሰርቶ እዚህ አድርሷል። ከላይ እንደጠቀስኩት፣ እንደ ዱላ ቅብብል ሩጫ፣ የሚቀጥለው አመራር ተቀብሎ፣ አሁን ካሉት ተምሮ፣ ያለው ላይ ጨምሮ ወደ ላቀ ቦታ ማህበሩንና ማህበርሰቡን እንድያደርስ ምኞቴ ነው።

# የማራዶናና የፔሌ ልዩነት


ተስፋዬ ቀነኒ
Tesfaye Keneni

ማራዶና

1. በግራው እግሩ ብቻ ይጫወታል
2. ታክቲካል የኳስ ምት አለው
3. በደረቱም ሆነ በእግሩ ኳስ ይቆጣጠራል
4. ሲያቀብል አስተካክሎና መጥኖ ነበር
5. 90% ኳስ አይስትም (ጎል)
6. አብዛኛውን የሚያገባው በእግሩ ነበር
7. ማራዶና የቱለና ተጫዋች ሆኖ በአብዛኛው የቀድምውን የሀንጋሪ ተጫዋች አጥቂ ፑሽካሽን ይመስላል
8. ማራዶና ክልስ (ኖቲቭ) ነዉ
9. ማራዶና የሜክሲኮ የአለም ዋንጫ ንጉስ ነው
10. ማራዶና ኳስ ጫዋታ የቆመው በመጥፎ ዝና ነበር
11. ማራዶና የዕፅ ሱስ ነበረበት
12. ማራዶና ባለታላቅ ሚሊየነር ነበር

ፔሌ

1. በሁለቱም እግሩ እኩል ይጫወታል
2. እጅግ የከረረ ጠንካራ ምት አለው
3. በደረቱም ሆነ በእግሩ በሚገባ ልክ ኳስን የቆጣጠራል
4. ሲያቀበልም መጥኖ ሲቀበልም በትክክል ይቀበላል
5. ፔሌ በአብዛኛው በቴስታ ግብ ያስቆጥራል
6. 99% ኳስ አይስትም
7. ፔሌ በጨቅታው ችሎታ ማንንም አይምስልም
8. ፔሌ የጥቁር ዘር ነው
9. ፔኤ የአለም ኳስ ንጉስ ነበር
10. ፔሌ በታላቅ ክብር ከኳስ አለም ተለየ
11. ፔሌ ምንም ሱስ አልነበረበትም
12. ፔሌ ባለትልቅ ክብር ነበር





# ስለሀበሻ ዩናይትድ ስፖርት ክለብ በጥቂቱ

ሃበሻ ዩናይትድ ክለብ የተመሰረተው June 8/2016 ሃበሻ ዩናይትድ የእግር ኳስ ክለብ በካልጋሪ ካናዳ የሚገኝ እድሜያቸው ከ6 እስከ 14 ዓመት የሆኑ ትውልደ ኢትዬጵያ ከሆኑ ቤተሰቦች የተወለዱ ህፃናትና ወጣት ልጆችን የእግር ኳስ ስልጠና የሚሰጥ ያለ ትርፍ የሚንቀሳቀስ ክለብ ነው። ይህ ቡድን የተመሰረተው በጥቂት ኢትዮጵያውያን ወላጆች በከተማችን ያለውን ካቅም በላይ የሆነ የእግር ኳስ ማሰልጠኛ ገንዘብና በገንዘቡ መጠንም የሚሰጠውን አነስተኛ ስልጠና በተሞክሮ በማያት ልጆቻችን እራሳችን ወላጆች ልናሰለጥናቸው እንችላለን በሚልና ከዛም በተጨማሪ ወደፊት እያደጉ ሲሄዱ በትምህርታቸው የተዋጣለት ነጥብ፣ በባህሪያቸው ጥሩ ኢትዮጵያዊንትን የተላበሰ ካናዳዊ ዜጋ ከዛም ባለፈ እርስ በራሳቸው የመጡበት ማህበረሰብ ተመሳሳይ በመሆኑ በሃሳብ እንዲተጋገዙ፣ በጓደኝነት እንዲቀራረቡና በየአቅማቸው እንዲተጋገዙ ለማሳደግ እንዲመች ታስቦ ነው። ሃበሻ ዩናይትድ የሚለው ስም ሊሰጠው የቻለ የቡድኑ አባላት የሆኑት ልጆች ተሰብስበው ክብዙ ስሞች አንዱን ማለትም ሃበሻ ዩናይትድ እሚለውን በቡዙ ድምጽ ስላጸደቁት ሲሆን ይሄን ስምም ማለትም ሃበሻ ዩናይትድን ለቡድኑ ስም እንዲሆን ያቀረበችው ብሌን ቴዎድሮስ ስትሆን ከJune 8/2016 ጀምሮ ቡድኑ ይሄን ስም እየተጠቀመ እሰከዛሬ ቆይቷል። ይህ ቡድን ከኢትዬጵያዊነት ውጭ የማንኛውም ሃይማኖታዊ ተቋም ወይንም ፖለቲካዊ ድርጂት ጥገኛ አይደለም በነዚህ ሁለት ነገሮች ተፅዕኖ ስር መሆንን አይፈቅድም። ቡድኑ በካናዳ ህግ መሰረት እውቅና ያለውና የሃገሪቱ ህግ መሰረት ሁሉን ነገር አሟልቶ ተመዝግቧል ። ስልጠና የሚሰጥበት ቦታ West Island College ሲሆን በዊንተር Indoor ዘወትር ቅዳሜ ከ3- 5 pm የእግር ኳስ ስልጠና ይሰጣል በ summer ደግሞ በዚህ አመት እንዳደረግነው Summer soccer camp በማዘጋጀት ሁለቱን የትምህርት ቤት ዝግ ጊዜአቸውን ወጣት አሰልጣኞችን በመቅጠር በአንድ ላይ ስልጠና እየሰጠ እንዲያሳልፉ ያደርጋል። የዚህ ቡድን የበላይ ተጠሪዎች አቶ ቴዎድሮስ አብርሃ (ግራንዴ) ና አቶ ህንፃ አሰፋ ናቸው እነዚህ ሁለት ሰዎች ከመስረታ እሰሰካሁኗ ስዓት ድረስ ደከመን ሰለቸን ሳይሉ ለሰባት ረጂም አመታት ቡድኑን እንዳይዳከም ከማሰልጠን እስከማስተባበር ድረስ እየረዱ ይገኛሉ።

# ስለ ማህበሩ ታሪክ ትዝ ከሚለኝ

ከ ዶ/ር አድማሱ አበበ

ጊዘው በፈረንጆች አቆጣጠር 2003 ነበር፡፡ የካልጋሪ የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ማህበር እንደገና እያንሰራራ መጥቶ የሰከነ አመራር አግኝቶ ወደፊት ለመራመድ የጀመረበት ወቅት ነበር፡፡ በዶ/ር አሉላ ፕረዚዳንትነት የሚመራው ቡድን (ዶ/ር ከተማ፣ ሚሊዮን፣ ዘላለም፤ ገሊላ ...ወዘተ) ቢሮ ከፍት ሆኖ አባላት አገልግሎት እንዲያገኙ ለማድርግ ይወስናሉ፡፡ እንደሰማሁት ቀደም ሲል የነበረው አመራር፣ በአባላቱ መካከል በነበረው የአገር ቤት የፖለቲካ ውጥንቅጥ (ኢህአፓ፤ መኢሶን ወዘተ) ነጠብራቅ አለመግባባቱ አይሎ የማህበሩ ፕረዚዳንት የነበሩት ሰው የቢሮ ቁልፍ ይዘው ብቻቸውን እንደሄዱ አልተመለሱም፡፡ ማህበሩን በዚህ ሁኔታ የተረከበው የነ ዶ/ር አሉላ ቡድን በ1997 ማህበሩን እንደገና አንሰራርቶ ቢሮ ለመከፈት የወሰነው በ2003 ላይ ነበር፡፡ በወቅቱ የማህበሩ ህገ ደንብ ጸድቆ፣ አባላት የፖለቲካ አቋዋማቸውን በየጉያቸው ይዘው በኢትዮጵያዊነታቸው ብቻ በማህበሩ እንዲሳተፉ እንዲጠይቅ ተደርጎ ነበር፡፡ ይህም ማህበሩ፤ አባላት ለውጥ ሊያመጡለት የማይችሉትን የአገር ቤት ፖለቲካ በየቡድናቸው ውስጥ እንዲገድቡትና፣ ማህበሩ፤ አባላት በስደት በሚኖሩበት አካባቢ የሚያጋጥማቸውን ማህበራዊ እክሎች የሚወጡባቸውን መንገዶች ወደማመቻቸት ስራ እንዲያተኩር አንደረዳው አገምታለሁ፡፡ በዚህ አኩዋሁዋን በፓርት ታይም ቅዳሜ ሙሉ ቀንና ሃሙስ ከ4 pm እስከ 8 pm አንድ ክፍል ባለው በ OLD Y COMMUNITY CENTRE ቢሮው ለመጀመሪያ ጊዜ ክፍት ሆኖ አገልግሎት መሰጠት ተጀመረ;; እኔም በወቅቱ የ3ኛ ደረጃ ትምህርቴን በሶሻልወርክ ጀምሬ ከኢሚግሬሽን ጋር የተያያዘ ጥናት እያደረግሁ፣ የቢሮውን ስራ በቅጥርና በበጎ ፈቃደኝነት ቅይጥ ለመቀጠር ተስማማሁ። ከ 2003 እስከ 2006 በሰራሁበት ወቀት በተለይ አዳዲስም ሆኑ ነባር አባላት ወደቢሮ መምጣት ጀመሩ;። አባላት ወርሃዊ ክፍያቸውን ለመክፈል፤ የስፖንሰርሽፕና ለሎች ጉዳዮችን ለመከታተል፤ ስለ አካባቢያቸው ጠቃሚ

መረጃዎችን ለማግኘት፡ ቀደም ሲል የስራ አስፈጣሚ አባላትን ለማነጋገር የነበረውን ችግር ለማቃለል የቢሮው መከፈት ጠቃሚ ሆኖ ተገኝቶ ነበር። እዚህ ላይ ሳልጠቅሰው የማላልፈው የኢቲዮጵያውያን ደግነት ሲሆን፣ ከአንድም ሁለት ጊዜ አንዳንድ አባላት በቅዳሜ ቀን ብቻህን ስለሆንክ ብለው ምግብ ያመጡልኝ ነበር። የቢሮው ለመጀመሪያ ጊዜ መከፈት አባላት ከማህበሩ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ከማሻሻሉም በላይ ማህበሩም ትናንሽ የትርጉም ስራ ለመንጃ ፈቃድ፤ የመዝናኛ የሃሳብ መለዋወጫ ምሽት በማዘጋጀት፤ በበጎ ፈቃደኞች የሚሰራ የታክስ አገልግሎች (ገነት መሃሪን ሃና አስራት)፤ ከኢትዮ ስታር የእግር ኳስ ቡድን ጋር በመሆን ዘፋኞችን በማስመጣት ለቡድኑ ገንዘብ ማሰባሰቢያ ዝግጅት በማድረግ፤ (ምንም እንኩዋን አንዳንዴ በመጠጥ የተነሳ አምባጓሮ ሲነሳ የነበረ ቢሆንም) በአፍሪካ ቀን ኢትዮጵያውያንን በማሳተፍ፤ በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ለሚማሩ ወጣቶች በውድድር የ$500 ድጋፍ በመስጠት፤ የስፖንሰርሺፕ ማመልከቻዎችን በስራ አስፈጻሚ አባላት አስገምግሞ በመንግስት ተቀባይነት የሚኖራቸውን ብቻ ለይቶ በማስተላለፍ ውድቅ የሚደረጉትን ማመልከቻዎች ቁጥር በመቀነስ አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቷል። የ"ህብረት" መጽሄትን በየወሩ አዘጋጅቶ በፖስታ ቤት ለአባላት መላክ፤ የህብረት ዝግጅት ቀደም ሲል በዶ/ር አሉላ ሲካሄድ የነበረ ሲሆን፣ በራኒ ሁሴንና በሳሙእል ታደሰ ሊቀመንበርነት ጊዜ ዝግጅቱ ሙሉ በሙሉ የኔ ሃላፊነት ነበር። በዚያን ጊዜ ቢሮእችን ወደ ሁለት ክፍል ቢሮ ተለውጧል። የአባላት ወርሃዊ መዋጮ $3 ስለነበረ ዋናው የማህበሩ የገቢ ምንጭ የካዚኖ ገቢ ብቻ ነበር። ለካዚኖ ጨዋታው ዋናው የበጎ ፈቃደኞች ምንጭ የኢትዮስታር ተጫዋቾችና ደጋፊዎቻቸው ነበሩ። ወርሃዊ መዋጮ የሚሰበሰበው በእጅ ደረሰኝ ሲሆን በሳሙእል ታደሰ ጊዜ ሲምፕሊ አካውንቲንግ የሚባል ሶፍትወር ተገዝቶ የገንዘብ አያያዙና አመዘጋገብ መስመር ያዘ። የየሳምንቱ ገቢ ቲዲ ባንክ ባለው የማህበሩ አካውንት ገቢ የማደርገው እኔ ነበርኩ። ከካዚኖ ከሚገኘው ገቢ የተወሰነውን ለቤት መግዣ ማስቀመጥ ቀደም ሲል የተጀመረ ሲሆን ይህም ቀጥሎ ነበር። ሌላው በዚህ ጊዜ የተከናወነው፤ ህጻናትን የአገራቸውን ፊደል እንዲማሩ የተደረገው ጥረት ነው Southern Alberts Heritage Language Association ከተባለው መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ከተገኘ ድጋፍ ኮምፒዩተርና ፕሮጀክተር ተገዝቶ ከሚሞሪያል ላይብራሪ ክፍል በመከራየት፣ የአማርኛ ፊደል ትምህርት በአንዲት ኢቶዮጵያዊትና በሁዋላም በዶ/ር ሙሉጌታ ገላው አማካኝነት መሰጠት ተጀምሮ ነበር፡፡ በመጨረሻ፤ የማህበሩን ቢሮ በማስተዳደር በሰራሁባቸው ጊዘያት የነበሩትን አመራሮች የገንዘብ አያያዝ ስነ ምግባርና ለማህበሩና ለአባላት የነበራቸውን ታማኝንት ለማድነቅ እወዳለሁ።

# ከዚህም ከዚያም

በአንድ መንደር ውስጥ ሥዕል እየሳለ በውድ ዋጋ በመሸጥ የሚተዳደር ሽማግሌ ነበር። ከእለታት አንድ ቀን አንድ የመንደሩ ነዋሪ የሆነ የኔ ቢጤ መጣና "አንተ ሠዓሊ ነህ፣ ሥዕል እየሳልክ ብዙ ስለምታገኝ ሀብታም ሆነሀል፤ ግን ለድሆች አትሰጥም፤ ባለ ልኳንዳ ቤቱ እንኳ ሁሌ ሥጋ ለድሆች በነጻ ያድላል።" አለው ሽማግሌው ሠዓሊም ፈገግ ከማለት ውጪ ምንም መልስ አልሰጠውም። ድህው ሰውዬም በመንደሩ እየዞረ ሽማግሌው ሀብታም እንደሆነና ግን ስስታም እንደሆነ አናፈሰ። የመንደሩ ሰዎች አዛውንቱን ጠሉት፣ ከጊዚያት በኃላ አዛውንቱ ታመመ። አንድ እንኳ የሚያስታምመው ሰው አጥቶ ሞተ። ከጥቂት ቀናት በኋላ ባለ ልኳንዳው ሥጋ ማደሉን አቆመ። ለምን ብለዉ የመንደሩ ሰዎች፣ የኔቢጤዉን ጨምሮ፣ መጥተው ሲጠይቁት፣ "እስከ ዛሬ የማድላችሁ እኮ ሠዓሊው ስለሚከፍለኝ ነው" ብሎ መለሰላቸው። ሁሉም እዉነታውን ሲያዉቁ፣ በጣም አዘኑ። አንዳንዴ ነገሮችን ሳናረጋግጥ ለውሳኔ አንቸኩል!

በ1981፣ በአንድ ሀገር አንድ ዶክተር ከጊዜው በፊት፣ ክብደቱ 1.5 ኪሎ ሆኖ የተወለደን ልጅ ህይወቱን ያተርፉለታል፤ ህጻኑ ልጅ በህይወት ተርፎ አድጎ የእሳት አደጋ ተከላካይ ሰራተኛ ይሆናል። ከ30 አመት ቡሃላ ሲወለድ ያዳነውን ዶክተር በመኪና አደጋ ምክንያት ዶክተሩ ሊቃጠል ሲል፣ ከሞት አድኖታል። ሰው መገናኛው አይታወቅምና ወዳጄ ለሰዉ ጥሩ ሁን።

<u>ከዘመኑ ስሞች ጥቂቶቹ</u>

1. ልማቱ ፈጠነ
2. ቦንድነህ አባይ
3. አኬልዳማ ታዬ
4. ፌደራል እርገጤ
5. ስልጣኑ በዛብህ
6. ግምገማ ከበደ
7. መብራት ይታገሱ
8. አክስዮን ሰብስቤ
9. ግብሩ ጫኛያለው
10. ቫቱ በዛብህ




The General and Electrical Contractors in 2021






The Assocation's Relief Aid for those Ethiopians affected by the war and unrest in the North and West part of the Country, 2022 and 2023




EC FUSION LOUNGE
EC FUSION + LOUNGE
SERVICES
FOOD ምግብ
BEVERAGE መጠጥ
ENTERTAINMENT መዝናኛ
LIVE MUSIC የሙዚቃ ዝግጅት
SPECIAL OCCASIONS ለተለያዩ ዝግጅቶች
EVENT SPACE BOOKING የቦታ ኪራይ አገልግሎት
HABESHA NIGHT
EVERY
FRIDAY & SATURDAY
አውታር
#207- 4909 17 Ave SE, Calgary
www.ecfusion.ca

